እንዳይደርስ በመፍራት ተሰደው እንዲቀሩ አድርጋችሁ የለምን?"

ዓመት፣ ዓመትን እየወለደ ኢንጂነሩ ከታሰሩ ከሥምንት ዓመት ከሁለት ወር በኋላ ተራ ወታደሮች ወደ እሥረኞች ይመጡና "ሁላችሁም ተለቃችኋል" ይሏቸዋል።

የእሥር መለቀቁ ዜና ሲመጣ ኢንጂነር ጌታቸው ከእነ ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ ጋር ሆነው ሻይ እየጠጡ እየተጨዋወቱ ነበር። ዜናው ግራ አጋባቸው። በስንት ታንክ የሚጠበቁ ሰዎች ድንገት "ተለቃችኋል ውጡ" ሲባሉ፣ መፈታት ብቻ ሳይሆን፣ ውጡ ብለው ሊያመልጡ ሲሉ ገደልናቸው ቢሉስ የሚል ጥርጣሬ ውስጥ ገቡ።

እውነት መሆኑን ከእሥረኞች መሃል ተጠሪያቸው ካጣሩ በኋላ ከግቢው ለመውጣት ቻሉ። በኋላ ግን ይጠብቋቸው የነበሩ ወታደሮች ሳይቀሩ እቃቸውን ተሸከሙላቸው።

በወቅቱ ጃንሜዳ ወስደው ነበር የለቀቋቸው። ሲለቀቁ ብዙዎቹ በእጃቸው ገንዘብ አልነበራቸውም። አንዳንዶቹ ቤተሰቦች ስለ እሥረኞቹ መፈታት የሰሙ ስለነበሩ ከቤተሰቦቻቸው መኪና መጥቶላቸው ሄዱ።

ኢንጂነር አንድ የሚያውቁት ጀኔራል ያገኟቸውና "በዚህ ተሳፍረህ ሂድ" ብሎ ገንዘብ ሰጣቸው። በዛ ተሳፍረው ወደ ባለቤታቸው እናት ቤት ሄዱ።

ሁሉ ነገር ተመሰቃቅሎ ነበር ያገኙት። ንብረት የለ፣ ቤት የለ። ባለቤታቸውን ከቤታቸው አስወጥተዋቸዋል። ለኪራይ እንኳን የሚከፍሉት ገንዘብ አልነበራቸውም።

ከዛም ለጊዜው ገነት ሆቴል አንድ ክፍል ተከራይተው መኖር ጀመሩ - ሥራ እስኪያገኙ ድረስ።





# ምዕራፍ አስራ አንድ
# በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሥራ ቆይታ

ኢንጂነር ጌታቸው ከእስር ቤት እንደተለቀቁ ሥራ መፈለግ ጀመሩ። የሥራ መጠየቂያ ማመልከቻቸውን ለሦስት መሥሪያ ቤቶች አቀረቡ። አንዱ ለUNHCR (ለተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን) ሌላው ለFAO (ለዓለም የምግብ ድርጅት) ሲሆን ሦስተኛው ለናይሮቢ ሃቢታት (Nairobi Habitat) ነበር።

ሥራ ለማግኘት ወርም አልፈጀባቸውም። መጀመሪያ ጠርቶ ያነጋገራቸው FAO ነበር። አዲስ አበባ ያለው የFAO ሃላፊ ቢሮው ጠርቶ በሰፊው አነጋገራቸው። "እንደ እናንተ ያሉ ባለሙያዎችና ሰፊ የስራ ልምድ ያላችሁ እዚህ እያላችሁ፣ ለምንድን ነው ከውጭ ሃገራት ባለሙያ ወደዚህ የሚመጡት?" የሚል አስተያየት ጣል አድርገው ነበር፤ የውጭ ሃገር ተወላጅ የሆኑት የሥራ ኃላፊው፣ በኢንጂነር ጌታቸው ሙያና የስራ ተሞክሮ በመደነቅ። ይህን ከተናገሩ በኋላ "በእርሶ ደረጃ ያሉ ባለሙያዎችን FAO ሲቀጥር እኛ አይደለንም እዚህ የምንወስነው። እዛው እሮም ያለው ዋናው መስሪያ ቤት ነው የሚወስነው" ካሉ በኋላ በሁለተኛው ቀን ኢንጂነሩን ጠርተው ያስገቡትን የስራ መጠየቂያ ማመልከቻና፣ የሥራና የትምህርት ሰነድ ወደ ሮም በመላክ እንድንቀጥርዎ እንዲፈቀድልን ጠይቀናል ሲሉ ገለጹላቸው።

ቀጥሎ የጠራቸው UNHCR ነበር። ኢንጂነሩ በተጠሩት መሠረት UNHCR በመሄድ ሃላፊው ቢሮ ገቡ። ኃላፊውም የሥራውን ባህሪይ አስረዳቸው። በማንኛውም ጊዜ ከውጭ ሃገራት የሚመጡ ዕቃዎች በጉሙሩክ በኩል ሲያልፉ ቁጥጥሩን የሚያደርጉት ኢትዮጵያውያኖች ሳይሆኑ የውጭ ሃገር ዜጎች መሆን ነበረ ባቸው። የጉምሩክ ውስጥ ሥራ የሚሠራው በአማርኛ ቋንቋ በመሆኑ ለቁጥጥሩ ሥራ የግድ ኢትዮጵያዊ ባለሞያ መቅጠር ስለተገደድን ልንቀጥርህ ተስማምተናል" በማለት ያለውን ሁኔታ ከገለፀላቸው በኋላ "አሁን በሥራው ላይ የተመደበው የውጭ ሃገር ዜጋ ስለሆነ ሊሠራው አልቻለም። ስለዚህ አንተ ሥራውን እንድትሰራው እንፈልጋለን። ደሞዝ የሚከፈልህም በዶላር ነው። እና ትስማማለህ ወይ?" ብሎ ጠየቃቸው። ኢንጂነር ጌታቸው ደሞዙ ከፍተኛ መሆኑን ተገንዝበዋል። ነገር ግን የደሞዙን ከፍተኛ መሆን በማየት ሞያቸው ባልሆነ ሥራ ላይ መቀጠሩ ሥራውን መበደል ብቻ ሳይሆን ስማቸውንም የሚአጎድፍ በመሆኑ ላለመቀጠር ወስነው ውሳኔያቸውንም እዛው ቢሮ ውስጥ እያሉ ለኃላፊው አሳወቁቸው።

የUNHCR ባለሥልጣን በኢንጂነር ጌታቸው አቋም በመደነቅ ወዲያውኑ ስልኩን ያነሱና ወደ ሊግ ኦፍ ሬድ ክሮስ ደወሉ። "ሃሎ ሚስተር ሆልቲ"፤ "ባለሙያ አግኝቼልሃለሁ። አሁኑኑ እልክልሃለሁ" አሉ። እሳቸውም ወዲያውኑ ሄደው አነጋገሩአቸው።

በዚህ መልኩ ነበር ኢንጂነር ጌታቸው ሥራቸውን በሊግ ኦፍ ሬድ ክሮስ የጀመሩት። እዚህ ድርጅት ውስጥ የሥራ መጠየቂያ ማመልከቻ አላስገቡም። ከአነጋገሯቸው፤ በኋላም በሦስተኛው ቀን ጠርዋቸው "የሊጉ አማካሪና የቴክኒክ ክፍል ሃላፊ ሆነህ እንድትሠራ ወስነናል" አሏቸው። ኢንጂነር ጌታቸውም በድርጅቱ





ውስጥ ለመሥራት ስምምነታቸውን ገለጹ። በዚህ ከፍተኛ የሥራ ደረጃ ሊጉ ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ሲቀጠር ይህ የመጀመሪያው ነበር።

ኢንጂነር ጌታቸው ሥራቸውን በሚገባ መሥራት ጀመሩ። ሥራው በምን መልኩ መሠራት እንዳለበት የሚያጠኑት እሳቸው ሆኑ። ከጄኔቫ ቀጥታ የሚመጣ ትዕዛዝም ነበር። ሥራው ተግባር ላይ በሚውልበት ጊዜ ግን በቀዳሚነት የቴክኒኩን ሥራ እሳቸው ነበር የሚሰሩት።

የሊግ ኦፍ ሬድ ክሮስ ቢሮ በቀይ መስቀል ግቢ ውስጥ ነበር የሚገኘው ምክንያቱም ፕሮጀክቱ በሶስቱም መ/ቤቶች በመቋቋሙ ነው። ሥራው በመሠረቱ ከUNHCR ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ነበረው። የዚህ ምክንያቱ የሁለቱም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በተለይም የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ትኩረታቸው ሥደተኛና ከስደት ተመላሾችን (Refugee and Returnee) የሚመለከት ስለነበረ ነው።

ኢንጂነሩ በሊግ ኦፍ ሬድ ክሮስ ቆይታቸው ሰፊ ጊዜያቸውን ወደ ኤርትራ የሚመለሱ ኤርትራውያኖችን መልሶ በማቋቋም ላይ አውለውታል። በአፄ ኃይለሥላሴ ጊዜ ተቃውሞ የነበራቸው ስደተኞች ከኤርትራ ተሰደው ነበር። እነዚህ ስደተኞች ከጎረቤት ሃገሮችና ከሌሎችም ሃገሮች ወደ ኤርትራ የተመለሱበት ወቅት ስለነበረ ለሰዎቹ ከብት፣ መሬት፣ የእርሻ መሣሪያዎችና እህሎች ይሰጣቸው ነበር።

ሌላው ትልቁ ሥራ የነበረው በጣሊያን ጊዜ ጣሊያኖች ያደራጁት አሊጊደር ውስጥ የሚገኘውን የመስኖ የእርሻ ማዕከል መልሶ ማቋቋምና አምራች ማድረግ ነበር። ከአርባ አምስት ሚሊዮን ዶላር በላይ በጀት በመመደብ የእርሻ መሣሪያዎችን በማስመጣትና የእርሻ

ባለሙያዎችን በሥራው ላይ በመመደብ እርሻው እንዲያንሰራራ ሊጉ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርጓል። ከጃፓንና ከሌሎች ሃገራት የመጡ የውጭ ሃገር ዜጎች በሥራው ላይ ተሳትፈዋል። ሥራውን በየጊዜያቱ ወደ ቦታው እየሄዱ የሚከታተሉትና ሥራው በወጣው እቅድ መሠረት መሠራቱን በክልሉ ከተመደቡት ኃላፊዎች በተጨማሪ ይመሩ የነበሩት ኢንጂነር ጌታቸው ነበሩ። ሠፈራውን የሚያዘጋጀው፣ ምግቡንና ከብቶቹን በፕሮግራሙ መሠረት የሚያድለው፣ እርሻውን ተግባር ላይ የሚያውለው ደግሞ የእርዳታ ማስተባበሪያ መ/ቤት ነበር።



ወደ ጋምቤላ በሚወስደው መንገድ ላይ (ቀርከሃ በብዛት ያለበት)

በሐረር በኩልም ከስደት ተመላሾችን መልሶ የማቋቋም ሥራና እርዳታ የመሥጠት ሥራ በሊጉ በኩል ይከናወን ነበር። ስራው ተግባር ላይ የሚውለው ደግሞ በእርዳታ ማስተባበሪያ ድርጅት





እና ከሌሎችም ጋር በመተባበር ነበር። ገንዘቡን የሚያቀርበው እና ሥራውንም የሚቆጣጠረው ሊጉ ሲሆን የቴክኒኩ ሥራ ቀጥታ የሚመለከታቸው ኢንጂነር ጌታቸውን ነበር። በጅጅጋም በኩል ተመሳሳይ ሥራ ሠርተዋል።

ኢንጂነር ጌታቸው በተግባርም በአስተሳሰብም ከጊዜያዊ መፍትሄ ይልቅ ዘላቂ መፍትሄን ይመርጣሉ። ለዚህም ይመስላል ለመጠለያም ሆነ ለመመገቢያ አገልግሎት ድንኳንን እንደ አማራጭ አድርገው የማይመለከቱት። ለምሳሌ ሐረር ውስጥ ከባቢሌ ገባ ሲሉ በስተቀኝ በኩል ያሠሩት መጋዘን እና ቢሮ እንዲሁም ስደተኞች ሲመጡ የሚመገቡበት፣ የሚታከሙበት ክፍሎች የተሠሩት በብሎኬትና በፕሪ ፋብርኬትድ ማቴሪያል ነው። ኢንጂነር ጌታቸው የፕሪ ፋብሪኬትድ ቤቶች ከውጭ አስመጥተው ለመጠቀም ስምምነት እንዲፈጠርም ሁኔታውን አመቻችተው ነበር።

እንዲህ እንዲህ ዓይነቱ የስራ አስተዋጽኦ በUNHCR በኩል ከፍተኛ ዕምነትን አስገኝቶላቸዋል። ቀድሞ ሲል ሊጉ በእርዳታ ማስተባበሪያ አሰራር ላይ የምንሰጠው ገንዘብ ይባክናል በሚል ቅሬታ ቢኖረውም በኢንጅነሩ አማካኝነት መግባባት ተፈጥሮ ሥራዎች በተሻለ መልኩ ሊሰሩ ችለዋል።

ኢንጂነር በሊጉ ውስጥ ባሳለፉት የሁለት ዓመት የሥራ ዘመን ለሥራ ያላቸው ፍቅርና ብቃት ከሊጉ አልፎ በሌሎች ተመሳሳይ ሥራን በሚሠሩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዘንድ ሥራቸውን በከበሬታ እንዲመለከቱላቸው አድርጓል። ይህም በኢንጂነር ጌታቸው ታታሪነትና የሙያ ብቃት ሲሆን UNHCR ከእሳቸው አለቃ ይልቅ እሳቸውን መርጦ ሥራውን እንዲሠሩለት ጥያቄውን ያቀረበው፤ እሳቸው ምንም ዓይነት የስራ ጥያቄ ማመልከቻ ለUNHCR ሳያቀርቡ ነው።

በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል፣ በUNHCR እና በሊግ የተቋቋመው ከስደት ተመላሾችና የስደተኞች ፕሮግራም እቅዱን ፈጽሞ ሲዘጋ ኢንጂነር ጌታቸውም የሥራ የምስክር ወረቀታቸውን ከሊጉ ወስደዋል። በዚህ መካከል የእሳቸው አለቃ የነበሩ ሰው በUNHCR እና በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል አዲስ በተፈረመው የስደተኛ ፕሮጀክት ውስጥ ለመሥራት ሥራ ይጠይቃሉ። በጊዜው በተለይ በሱዳን በኩል የእርስ በርስ ጦርነቱ በጣም ተፋፍሞ ስለነበር በርካታ ሱዳናውያን በUNHCR እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ የሥራ ጫና ፈጥሮ ነበር።

የኢንጂነሩ አለቃ የነበሩት የኖርዌጅያ ተወላጅ የሥራ ጥያቄ ለUNHCR ሲያቀርቡ፣ ከUNHCR የተሰጣቸው መልስ አንተን አንቀጥርም ብቻ ሳይሆን፣ መቅጠር የምንፈልገው ኢንጂነር ጌታቸውን ነው የሚል ነበር። ባጭሩ "እኛ በጋምቤላና በሌሎች ቦታዎች ለሥራችን የፈለግነው ኢንጂነር ጌታቸውን ነው።" አሏቸው። ቀደም ብሎ UNHCR ከሊግ ጋር በሠሯቸው ሥራዎች፣ በተለይ በህክምናው መስክ፣ የኢንጂነር ጌታቸውን የሙያ ብቃትና የሥራ ትጋት ያውቃሉ።

የኖርዌይ ተወላጅ የሆኑት የኢንጂነሩ አለቃ የUNHCR ምርጫ ምን እንደሆነ ሲያውቁ ወደ ኢንጂነር ጌታቸው ይመጡና "አቶ ጌታቸው እኔ በUNHCR ሥራ ለመቀጠር አመልክቼ ነበር። እነሱ ግን አንተን ነው የመረጡት። ስለዚህ እኔ በአንተ ሥር ሆኜ ለመሥራት እፈልጋለሁና አግዘኝ" ይሏቸዋል።

"አይ እኔ የበላይ ሆነው ሲሠሩ የቆዩትን ሃላፊ ከእኔ በታች ሆነው ይስሩ ብዬ ለማለት አልችልም። ባይሆን እርስዎ የበላይ ይሁኑና እኔ ከእርሥዎ ሥር ሆኜ እሠራለሁ" ይሏቸዋል።





ሰውዬው ኢንጂነር ያሏቸውን ሄደው ለUNHCRና ለኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ኃላፊዎች ያሳውቋቸዋል። ኃላፊዎቹም የሰውዬውን ሃሳብ አልተቀበሉም። አሁንም ምርጫቸው ኢንጂነር ጌታቸው መሆናቸውን በድጋሚ ያሳውቋቸዋል። ሰውዬው ቁርጣቸውን ሲያውቁ ጓዛቸውን ጠቅለው ሃገራቸው ገቡ።

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀልና የUNHCR ኃላፊዎች ኢንጂነሩ ቦታውን እንዲይዙ ይነግሯቸውና ወደ ጋምቤላ ሄደው ሥራውን ተረክበው በአዲስ መልክ ቀጠሉ።

ዋናው የመጀመሪያ ሥራቸው የሕክምናውን ክፍል ማቋቋም፣ ሥራን ማከናወን፣ ስደተኞች ተገቢውን ህክምናና ምግባቸውን እንዲያገኙ ማስቻል እና መቆጣጠር ነበር። አለቆቻቸው በሥራ ጥራታቸው ስለረኩ የአስተዳደሩን ሥራ በአጠቃላይ በበላይነት እንዲመሩ ኃላፊነቱ ተሰጣቸው።

መጀመሪያ የሄዱት ኢታንግ ነበር። ስዊዲኖች ቀደም ብሎ በሆስፒታል ውስጥ መለስተኛ እርዳታ ከማድረጋቸው ውጭ ሌላ አገልግሎት አልነበራቸውም ለዚሁ ፕሮጀክት ተፈላጊ የሆኑትን ቁሳቁሶች በእርዳታ የሚያቀርቡት ወርልድ ፉድ ፕሮግራም ምግብን፣ MSF መድኃኒትን፣ ሉትራን ወርልድ ፌዴሬሽን የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮን፣ ጂቲ ዜድ ትራንስፖርት አገልግሎትን ሲሆን እርዳታ ማስተባበሪያ ደግሞ ስደተኞችን መዝግቦ መቀበልና ምግብና ቁሳቁሶችን ማከፋፈል ነበር።

እነዚህ ድርጅቶች ሁሉ ኢንጂነር ጌታቸው ማኅተመሥላሴ ለሚመሩት ፕሮጀክት ድጋፍ ሰጪ እና እርዳታ አቅራቢ ግብረ ሃይል ድርጅቶች ነበሩ። ለዚህም ፕሮጀክት አስፈላጊውን በጀት አዘጋጅቶ

የሚያቀርበው የኢንጂነር ጌታቸው መ/ቤት ነበር።

ኢንጂነር ጌታቸው ጋምቤላ ኢታንግ ላይ በተመደቡበት ወቅት ከሕክምና መስጫ ጀምሮ መመገቢያው፣ መኖሪያው፣ መጋዘኑ፣ ምግብ ማብሰያው፣ አስተዳደሩ ወዘተ በጠቅላላ በድንኳን ሥር ነበር የሚከናወነው። ድንኳን ውስጥ ይሰጥ የነበረውን አገልግሎት አስቁመው ወደ ኮንስትራክሽን ሥራ በመሸጋገር አገልግሎቱ ከድንኳን ወደ ዘመናዊ ቤት እንዲለወጥ አደረጉ።

በዛው ወቅት ሌሎች ጣቢያዎች በፉኚዶና በአበቦ ቀጠለ። ይሄ ሁሉ የሥራ ሃላፊነት የኢንጂነር ጌታቸው ሆነ። በሁሉም ቦታ ህክምና መስጪያውንና ሠፈራ ጣቢያውን በዋናነት አቋቋሙ።

የሃኪሞች መኖሪያ ተሠራ፣ የፀሃፊዎችና የአስተዳዳሪዎችም ቤቶች ተገነቡ። ክሊኒክ ሳይሆን ሆስፒታል ተሠራ። "አዲስ አበባ ውስጥ እንዳሉት ዓይነት ህንፃ አሠራሁ" ይላሉ ኢንጂነር ጌታቸው በልበ ሙሉነት። ለስደተኞች ማስተናገጃ ከመጣው በጀት ላይ ለድንኳኖች መግዣ የሚወጣውን በጀት ወደ ቋሚ ንብረት ለማዛወር በቂ ምክንያት ማቅረብ ነበረባቸው፤ ሲያብራሩም አንድ ድንኳን አገልግሎት የሚሰጠው ቢበዛ ለ2 ዓመት ነው ምክንያቱም በነፋስ ይገነጠላል፣ አይጥ ይበላዋል፣ ከመጋዘን ቁሳቁስ ለመስረቅ ቀደው ይገባሉ፣ በቆላማ አገር ተገቢ ምቾት አይሰጡም ስለዚህ ይህን ተደጋጋሚ ወጭ ከማውጣት ከድንኳኖቹ ወጭ ባልበለጠ ገንዘብ ቋሚ ንብረት ልሥራ ብለው ለፕሮጀክቱ ኃላፊዎች አቅርበው አስፈቀዱ። ያላቸውን የምሕንድስና ሞያ በመጠቀም ድንጋዩን፣ አሸዋውን ሌላም ቁሳቁሶች በነፃ ከአካባቢው በመሰብሰብ እንዲሁም ባለሞያና የቀን ሠራተኞች ከስደተኞቹ በመጠቀም እቅዳቸውን በማሳካት አሁን በወረዳ ከተማነት





የሚያገለግሉ ከተሞች መገንባት ችለዋል። በተለይም ሆስፒታል፣ የሐኪሞች መኖሪያ፣ የእህል ወፍጮዎች፣ የኤሌክትሪክ ሞተሮች፣ ከ3000 ኩንታል በላይ የሚይዙ መጋዘኖች፣ የሕመምተኞችና የሕፃናት መመገቢያ አዳራሾች፣ የሠራተኛው ዘመናዊ ካንቲንና ሌሎችም ለከተማው ተመራጭነት አስተዋጽኦ አድርገዋል። የመኪና መንገዱም ለክረምትና በጋ እንዲያገለግል ሁኖ የተሠራው በኢንጂነር ጌታቸው ጥረት መሆኑን ገልፀዋል።

እነዚህን ዘላቂነት ያላቸውን አገልግሎት ሰጪ ግንባታዎች ሲያሠሩ መንገዱ አልጋ በአልጋ አልነበረም። በዕርዳታ የሚመጣውን ገንዘብ ወደ ኪሳችን ካላስገባን የሚሉ የውጭ ሃገር ዜግነት ያላቸው ፕሮግራም ኦፊሰሮች ችግር ሊፈጥሩባቸው ሞክረዋል።

ለሰሩዋቸው ሥራዎች አድናቆታቸውን የሚለግስዋቸውም ሰዎች ነበሩ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ አቶ መንገሻ የሚባሉ ፕሮግራም ኦፊሰር ሲሆኑ፣ "እንደው ኢንጂነር ጌታቸው ይህን ሁሉ ሥራ የምትሰራው ገንዘቡን ከየት እያመጣኸው ነው? እንዴትስ ተብቃቃልህ?" ሲሉ በአንድ ወቅት ጠይቀዋቸዋል፤ የሚገኘውን የእርዳታ ገንዘብ በጥንቃቄ ሥራ ላይ ማዋላቸውን በማጤን።

ከውጭ ሃገራት ሰዎችም እንግሊዛዊው ም/ኮሚሽነር ሚ/ር ፌል የሠሩዋቸውን ሥራዎች በመመልከት "እንዴት ያለህ ጥሩ ሰው ነህ" ብለዋቸዋል። እንደዚሁም ከሚ/ር ፌል በፊት በሥራው ላይ የነበረ አንድ አውስትራሊያዊ ም/ኮሚሽነር "ስማኝ" ይሏቸዋል "እነዚህ የእርዳታ ማስተባበሪያ ሰዎች ገንዘቡን በአግባቡ አልተጠቀሙበትም፣ አንተ ግን በሚፈለገው ቦታ ላይ አዋልከው" በማለት አመስግነዋቸዋል።

በወቅቱ ችግር የሚፈጥሩት ሁለት ፕሮግራም ኦፊሰር አፍሪካ

ውያኖች፣ ምክትል ኮሚሽነር የነበረች አንዲት አፍሪካዊት እና ቀደም ብሎም አንድ እንግሊዛዊ ነበር፡፡

የእነሱ ቀዳሚ ዓላማ ለእርዳታ የመጣውን ገንዘብ ለምን እኛው አልተቀራመትነም? የሚል ስሜት ስለነበራቸው ይሄን ዓላማቸውን እንዳያሳኩ ኢንጂነር ጌታቸው እንቅፋት ሆኑባቸው፡፡ “ለምንድን ነው እኛ ሳናውቀው ገንዘቡን ሥራ ላይ የምታውለው?” የሚል ጥያቄ ደጋግመው አንስተውባቸዋል፡፡

በአንድ ወቅት በኢንጂነር ጌታቸው እንቀፋት መሆን የተናደደችው ኮሚሽነርዋ “ይህንን ነገር በጋዜጣ እናወጣዋለን” እስከማለት ደረሰች፡፡ ይሄኔ ኢንጂነር በንግግርዋ ይስቁባታል፡፡ ስለተሳቀባትም በጣም ተናደደችና “እኛ በምንናገረው፣ አንተ ትስቃለህ” ትላቸዋለች፡፡ “ታዲያ ላልቅስልሽ ወይ?” በማለት ይበልጥ እንድትናደድ አደረጓት፡፡

ኢንጂነሩ ባላቸው ንፅህናና ቆራጥነት ስለገፉበት እንዲሁም በምንም ዓይነት የማይበገሩ መሆናቸውን ሰዎቹ ሲገነዘቡ ወደ እሳቸው እየቀረቡ መምጣት ጀመሩ፡፡

በሌላ ጊዜ በጄኔቭ የሚገኘው ዋናው የስደተኛ ጉዳይ ሃላፊ ሥራዎቹን ለመመልከትና ለመገምገም ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ፡፡ አፍሪካውያኖቹ የፕሮግራም ኦፊሰሮች ይህን አጋጣሚ በመጠቀም “ጌታቸው የውጭ ሃገር ዜጎች እዚህ ሃገር ውስጥ ተቀጥረው እንዲሰሩ ፈቃደኛ አይደለም፡፡ ጥላቻ አለው” በማለት ለተሰብሳቢዎቹ አሳወቁ፡፡

ይህንን የፈጠራ ታሪክ ከሰሙት ውስጥ የናይጄሪያው አምባሳደር አንዱ ሲሆኑ በቀጥታ ኢንጂነር ጌታቸውን “አንተ ለምን የውጭ ሃገር ሰዎችን ጠላህ?” በማለት ይጠይቋቸዋል፡፡ ኢንጂነር ጌታቸውም





መልስ አልሰጧቸውም፡፡

የእንግሊዝ አምባሳደርም ወደ ኢንጂነር ጌታቸው ቀረብ ብለው “አንተ ለምንድን ነው እንዲህ ዓይነት የከረረ ጥላቻ በውጭ ሰዎች ላይ ያለህ?” በማለት ሲጠይቋቸው፤ ኢንጂነር በተረጋጋ መንፈስ እንግሊዛዊው አምባ ሳደር ለጠየቋቸው ጥያቄ የሰጧቸው መልስ “እኔ በማንም ላይ ጥላቻ የለኝም፡፡ ዋናው ጉዳይ ለእርዳታ የሚመጣውን ገንዘብ እነሱ ይበሉታል፡፡ ይሄ ነገር መሆን የለበትም፡፡ ለምሳሌ አንድ የውጭ ሃገር ሰው ወደዚህ ሲመጣ መኪና መስጠት አለ፣ ቤት መስጠት አለ፣ የቀን አበሉ ከፍተኛ ነው፣ ከውጭ ሃገር ሲመጣ በተወሰነ ጊዜ ወደ ሃገሩ ለእረፍት የመሄጃ ትራንስፖርት አለ ይሄ ይሄ ሁሉ ከፍተኛ ወጪን ይጠይቃል፡፡ ከውጭ ሃገራት ከሚመጡት ባለሙያዎች ይልቅ እዚህ ኢትዮጵያውያኖች ቢቀጠሩ ግን እነዚህ ሁሉ ወጪዎች አይኖሩም፡፡ ስለዚህም የመጣው እርዳታ ይበልጥ ለእርዳታ ፈላጊው ህዝብ ይደርሳል፡፡” ብለዋቸዋል፡፡

አምባሳደሩ በጥሞና አዳምጠው አጭር ቃል ብቻ ነበር የተናገሩት “ኢንጂነር ጌታቸው ትክክል ነህ” ነበር ያሉት፡፡ ይህን ከኢንጂነር ጌታቸው የሰሙትን ገለፃ ለሃላፊው አንድ በአንድ እንደሚነግሯቸው ኢንጂነሩ እርግጠኛ ነበሩ፡፡ ከዚህ በኋላም ነበር በእርሳቸው ላይ ጥላቻ እንዲኖር ቅስቀሳ ያደርጉ የነበሩት ፕሮግራም ኦፊሰሮች አንገታቸውን በመድፋት ፀጥ ያሉት፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያውያን ኤክስፐርቶችን መቅጠር አስፈላጊ ሆነው ሲያገኙት በብዛት መቅጠር ጀመሩ፡፡

ከጄኔቫ የመጡት ሃላፊ ፋኚዶ ላይ በኢንጂነር ጌታቸው ጥረት የተሠራውን ሆስፒታል ሲመለከቱ እጅግ ተደሰቱ፡፡ ሆስፒታሉ አዲስ

አበባ ካሉ አነስተኛ ክሊኒኮች የሚስተካከል ነበር፡፡ የምርመራው ክፍል፣ የመድሃኒቱ ክፍል፣ የመኝታው ክፍል፣ የሴት ታማሚዎች ክፍል፣ የወንድ ታማሚዎች ክፍል... ሁሉም ያማረ ሆኖ ተሰ ርቷል፡፡ የቀረው መስታወት ብቻ ነበር፡፡ እሱም ቢሆን (በነጭ ጆንያ) ተወጥሮ ስለነበር መስታዎት ይመስል ነበር፡፡

ሃላፊው ጉብኝት ከማድረጋቸው በፊት ሁለቱ አፍሪካውያን ፕሮግ ራም ኦፊሰሮች ከኢሉባቦሩ አስተዳዳሪ ጋር በመሆን ክሊኒኩን ጎብኝተው ነበር፡፡ ክሊኒኩ እንዲህ ያማረ፣ የተቀላጠፈና የተሟላ አገልግሎት ሊሰጥ በሚችል ደረጃ ይሰራል ብለው አልጠበቁም፡ ፡ ተናደዱ፡፡ ለመሳደብም ፈልገው ነበር፡፡ ለሃላፊዎቹ ነግረዋቸው ከነበሩት ወሬዎች ጋር ሁኔታው ተጣረሰባቸው፡፡ ሥራ አልተሠራም ብለው ያሳበቁ ይመስላሉ፡፡ "አንተ ተአምር ትሠራለህ፣ ሥራውን ስትሠራ ለእኛ ለፕሮግራም ኦፊሰሮች ያላሳወቅከው እኛ እንድንወቀስ ነው?" በማለት ወደ ዘለፋም ለመግባት ሞክረው ነበር፡፡

ኢንጂነር ግን እዛው ላይ "እኔ ከየሜዳው ተለቃቅሜ የመጣሁ ባለሙያ አይደለሁም፡፡ እኔ ሥራዬን የማውቅ ሰው ነኝ፡፡ ሥራዬን በፕሮግራም ነው የምሠራው" በማለት መልስ ሰጥተዋቸዋል፡፡ ሰዎቹ መልስ አልነበራቸውም፡፡ በዛ ላይ በተሠራው ሥራ ሃላፊው እጅግ መደሰቱን ተመልክተዋል፡፡

ይህም ሥራቸው ይበልጥ ተፈላጊ እንዲሆኑ አደረጋቸው፡፡ በየቦታው የሚጠሩት እሳቸው ብቻ ሆኑ፡፡ አሶሳና ሃረርም የUNHCR ፕሮጀክት ሲከፈት ሥራውን እንዲያቋቁሙ የተፈለጉት እሳቸው ሆኑ፡፡

ለአገር ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጡት ኢንጂነር ጌታቸው ብዙ እቅዶችን ነድ ፈው ነበር፡፡ ለምሳሌ የእርዳታ እህል በቆሎ እና ስንዴ በከፍተኛ






የትራንስፖርት ወጪ ከውጭ አገር ተጭኖ ነበር የሚመጣው፡፡ ኢንጂነር "ለምንድን ነው እህሉን ከሃገር ውስጥ የማንገዛው? ከውጭ ተገዝቶ ሲመጣ ወደ ሃገር ለማምጣት የትራንስፖርት ወጪ አለ፡፡ እህሉን ወደ መሃል ሃገር ለማጓጓዝ ተጨማሪ የትራንስፖርት ወጪ አለ፡፡ ይሄ ሁሉ ወጪ በከንቱ ነው የሚወጣው ስለዚህ እህሉ ለምን ከሃገር ውስጥ አይገዛም?" በማለት ሃሳብ አቀረቡ፡፡

ይህን ሃሳብ ያቀረቡት ገንዘቡ እዚህ ሃገር ውስጥ እንዲወጣ ገበሬዎችም በደህና ዋጋ ገዥ እንዲአገኙ ነው፡፡ እርሻንም ለማስፋፋት ይጠቅማል በማለት ነበር፡፡ በእርግጥም እህሉ እዚህ ሃገር ውስጥ እንዲገዛ ተፈቀደ፡፡

ኢሉባቦርንና ከፋን የሚያገናኝ ድልድይ የማሰራት ውጥንም ነበራቸው፡፡ ኢሊባቦር ውስጥ ሰፊ በመስኖ መልማት የሚችል ቦታ ስለነበር እሱን ለማልማት በማሰብ ነበር ሃሳቡ የቀረበው፡፡

በተጨማሪም በአካባቢው አውሮፕላን ጣቢያ አልነበረም፡፡ ለUNHCR ለምን የአውሮፕላን ማረፊያ እዚህ ላይ አንሠራም፣ እህልና ሌሎች እርዳታዎችንም ለማጓጓዝ ይጠቅመናል ብለው ሃሳብ አቀረቡ፡፡ በሐሳቡ ተቃውሞ አልነበረም፡፡

ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ በመሄድም ቦታ እንዲመርጡና ስራውን እንዲያጠኑላቸው ጠየቁ፡፡ በአየር መንገድ ባለሞያዎች ቦታው ተመርጦ ፕሮጀክቱ ባለው ቡልዶዘር ቦታውን ማስጠረግ ተጀመረ፡፡ ከወረዳው አስተዳደር አንዳንድ ሰዎች አየር መንገዱ ያጠናውን ቦታ ካዩ በኋላ የተሻለ ቦታ አለ፣ በማለት ሥራው እንዲጓተትና በኋላም እንዲቆም አደረጉት፡፡ የእሳቸው እቅድ የመስኖ ልማቱም ሆነ የአውሮፕላን ማረፊያው እንዲከናወን ያሰቡት ከእርዳታው በሚገኝ ገንዘብ ነበር፡፡



በክፋ ዲማ በኢንጂነር መሪነት የተሠራው የስደተኞች ጣቢያ ሕንፃ

በUNHCR ቆይታቸው ከሠርዋቸው ሥራዎች መካከል ከፍተኛ እርካታ ያገኙበትን ሥራ ሲናገሩ፡- “ስደተኞቹ ልብስ፣ ምግብና የተሟላ ህክምና ሲቀበሉና አገልግሎት ሲያገኙ በፕሮጀክቱ አካባቢ የሚኖሩት ኢትዮጵያውያኖች እየተመለከቱ ነው። እንዲህ ዓይነት እርዳታ ስደተኛ በመሆን የሚገኝ ከሆነ ሰዎቻችን እንዲሰደዱ ስለሚገፋፋቸው፣ ለምን ሌላው ቢቀር እንኳን እዚሁ ነፃ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ አናደርግም” በማለት ለሃላፊዎች አስታውቀው ኢትዮጵያውያኖች ነፃ ህክምና እንዲያገኙ አስፈቅደዋል። ሰዎቹ ከአካባቢው ብቻ ሳይሆን ከሌላ ከተማ ጭምር እየመጡ ህክምናና መድሃኒት በነፃ እንዲያገኙ አድርገዋል።

ሌላው ጥርጊያ የነበረውን መንገድ የአስፋልት መንገድ እንዲሆን በUNHCR እንዲሠራ አድርገዋል። መጀመሪያ ላይ ለአቶ ካሳ ገብሬ ይጽፋሉ። “ቦታው ጠረፍ ነው። አንድ ችግር እንኳን ቢፈጠር





ለመንቀሳቀስ አይመችም። ስለዚህ አውራ ጎዳና ዲዛይን ቢዘጋጅልን” ብለው ጠየቁ። ወዲያው ቦታው እንዲጠና ተደረገና ጥናቱ ተሳከ ላቸው። መንገዱም በክረምትና በጋ የሚያስኬድ ሁኖ የጠጠር መንገድ ከበበቃ ተነስቶ እስከ ፉኚዶ በደንብ እንዲሠራ ተደረገ። መንገዱም እስካሁን ድረስ እያገለገለ ይገኛል።

በመሠረቱ ስደተኛው በአብዛኛው የኢኮኖሚ ስደተኛ ነው ማለት ይቻላል። ጠሩም ቢሆን የጦር ጉዳተኛውን ስደተኛ ነው በማለት ወደዚህ ይልኩ ነበር። የጦር ሥደተኛው እንዲያገግምና ታክሞ ሲጨርስ “መልሰህ ላከው” የሚል አንድ በጽሑፍ የተዘጋጀ ማስረጃ በአንድ አጋጣሚ እጃቸው ገባ።

የስደተኞች ሃላፊ እዛው ነበር። “ማስረጃ አግኝቼብሃለሁ።” ይሉና ያሽማ ቅቁታል። በእሱ ላይ ያላቸውን ቁጥጥርና የበላይነትም አጠናከሩ። የሚፈል ጉትንም ነገር እንዲፈጽምላቸው ለማድረግ መረጃው ጠቅሟቸዋል።

ስደተኞቹ የሚፈጥራቸው ብዙ ችግሮችም ነበሩ። በአካባቢው በዱር አውሬዎች ላይ ከፍተኛ ዘመቻ በማካሄዳቸውና እየገደሉ መብላት በመጀመራቸው የዱር አራዊቱ ወደ ጎረቤት ሃገር እንዲሰደዱ ምክንያት ሆኑ።

ሰዎቹ ቤታቸውን፣ አልጋቸውን የሚሰሩት የአካባቢውን ደን በመጨ ፍጨፍ ነበር። ደኑን ለማገዶም ይጠቀሙበት ስለነበረ ደኑ እየተመናመነ ሄደ። አካባቢው ወደ በረሃነት እንዲለወጥ አደረጉት። ኢንጂነሩ ይህን ጥፋት ማቆም አለብን በማለት የችግኝ ጣቢያ አቋቋሙ “ሌላው ቢቀር ችግኙን እየወሰዳችሁ ትከሉ” በማለት ለስደተኞቹ ትዕዛዝ አስተላለፉ።

የዛፎችንም ጭፍጨፋ ለመቀነስ በአከባቢው የሱዳን ሣር የሚሉት "ደገላ" የሚባለውን ሣር ለማገዶ አገልግሎት እንዲውል ሃሳብ ለUNHCR አቀረቡ። ሣሩ እስከ ሦስት ሜትር ማደግ ይችላል። "ደኖችንን ጨፍጭፈው ሳይጨርሱት እንደ አንድ መፍትሄ የሚታየኝ የደገላ ሣሩን ሥራ ላይ ማዋል ነው። ሣሩ ተቆርጦ ይከተፍና በማሽን በመጠቅጠቅ እንደ ከሰል ማድረግ ይቻላል። በዚህም ደኖች እንዳይጨፈጨፉ፣ ዛፎች እንዳይቆረጡ ይረዳል። ሣሩ ትከሉኝ፣ ውሃ አጠጡኝ አይልም። በየሙቱ ጊዜውን ጠብቆ ይበቅላል" በማለት ጠቀሜታውን በማስረዳት ለUNHCR ፊዩል ብርኬት ከሚሠራው ማሽን ጋር አቅርበው በጆት ጠይቀው ነበር።

እነዚህ ሁሉ ጠቃሚ ሥራዎች እየተሠሩ ባለበት ሁኔታ "የሥደተኞች ጉዳይ ከፖለቲካ ጋር ግንኙነት ያለው ጉዳይ ነው" በሚል የደርግ መንግሥት ከኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ጋር የነበረውን ስምምነት ተሠርዞ ሥራው ከደህንነት ሚኒስቴር ጋር የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች አስተዳደር በሚል አዲስ ስምምነት ከUNHCR ጋር እንዲፈረም ተደረገ።

በላያቸውም ላይ አንድ ኮሎኔል አምጥተው ሾሙባቸው። በማስከተልም እሳቸው የቴክኒክ ክፍል ሃላፊ ብቻ እንዲሆኑ በማድረግ "ከእንግዲህ አንተ የመንግሥት ሠራተኛ ነህ" ተባሉ።

ሥራውን መውሰዳቸውም ስለ ስደተኞቹና ስለተመላሾቹ አስተዳደር ብቻ ሳይሆን የአካባቢውን ሁኔታም ለማወቅ ጠቅሟቸዋል። የሳቸው ኃላፊነት ከሁሉም ክፍሎች ጋር ግንኙነት ያለው በመሆኑ ከእርዳታ የሚመጡ ቁሳቁሶች በሚከፋፈሉበት ጊዜ በመንገድ ላይ የሚቀረውንና ከየመጋዘኑ የሚባክነውን የሚያዩ እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች በተለይ





ወርልድ ፉድ ፕሮግራም በርስዎ ክፍል ብክነት አለ፤ ሲያዙም ሾፌሩ ነው እንባላለን ይሉኛል። ሹፌር ከኃላፊዎች፣ ከተረካቢዎችና ከአከፋፋዮች ካልተስማማ ብቻውን ድርጊቱን መፈፀም አይችልም። ይባስ ብሎ መኪና ጭምር ጠፋ ከዚህ በኋላ ነገሩን መቆጣጠሩ ከአቅሜ በላይ ሆነ በማለት መልካም ስማቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ሥራቸውን በፈቃዳቸው ለመልቀቅ ተገደዱ።

WFP ኢንጂነሩ በደርግ ባለሥልጣኖች ዘንድ በጥርጣሬ መታየታቸውን አልተገነዘበላቸውም። የደርግ ባለሥልጣኖች በየስብሰባው ላይ በዓይነ ቁራኛ ይከታተሏቸውም ነበር።

ኢንጂነር ጌታቸው ነገሩ ስላላማራቸው በመጨረሻ ጡረታቸውን በመጠየቅ የስራ መልቀቂያ እንዲሰጧቸው ጥያቄቸውን አቀረቡ። የተሰጣቸው መልስ ደሞዝህ በእርዳታ ከሚሰጥ ገንዘብ ስለሆነ የሚከፈልህ ፕሮቪደንት ፈንድ ነው በማለት በመንግስት ሠራተኝነት ከፍተኛ ጡረታ እንዳያገኙ ከልክለው አሰናበቷቸው።

የጡረታ መብታቸውን ግን እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ በነበረው የአገልግሎት ዘመን እንዲወሰን ተደረገ።

# ምዕራፍ አስራሁለት
# ኢንጂነር በጃክሮስ ኢትዮጵያ

ከUNHCR እንደለቀቁ ጃክሮስ የተባለው የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሥራ የኮንስትራክሽን ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ስለ እሳቸው የሙያ ብቃት መረጃውን ከየት እንዳገኘ አይታወቅም ብቻ "ኢንጂነር ጌታቸው ብዙ ሥራዎች አሉኝ። እኔ ደግሞ እዚህ ብዙ አልገኝም። እርስዎ ሥራዎቹን በምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅነት ደረጃ ሆነው ሥራዬን በትጋት እንዲሰሩልኝ" በማለት ጥያቄ አቀረበላቸው። ደሞዙም ጥሩ ስለነበር ስራውን ጀመሩ።

ሥራው በምንና በየት አቅጣጫ መጓዝ እንዳለበት የሚወስኑት እሳቸው ሆኑ። በተለይ ሴትልመንቱን (አቀማመጡን)፣ ቤቶች እንዴት መሠራት እንዳለባቸው፣ መንገድ አውታሮችን በየት በኩል መውጣት እንዳለበት ለመሃንዲስ ክፍሉ መመሪያ በመስጠት ሁሉንም መስመር በማስያዝ አስተካከሉ።

ግን ችግር ነበረው። አንደኛ ድርጅቱ ሲጀምር ብቃት ያላቸው ሠራተኞች አልነበሩትም። የተወሰኑ ቢኖሩም ቴክኒሻኖቹ በጎን የራሳቸውን ኩባንያ አቋቁመው የጃክሮስ ሥራ ተቋራጭ በመሆን እነሱ በወሰኑት ዋጋ ለጃክሮስ ሥራ የሚገዙ ዕቃዎችንም ጭምር ወደ ራሳቸው ኩባንያ ገቢ እንዲሆን በማድረግ ይሰሩ ስለነበር ጃክሮስም እራሱ እዚህ ሃገር ውስጥ የሚዘልቅ ስላልመሰለው፣ በውጭ ሃገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያኖች ቤት እሰራላችኋለሁ እያለ የሚቀበላቸውን ገንዘቦች የት እንደሚያደርገው ስለማይታወቅ





ለሊዝ መክፈል የሚገባውን ገንዘብ በጊዜው ስለማይከፍል፣ ታክስ የሚጠይቀውም አካል ስላልነበረ ቤትም እሰራለሁ እያለ ለመሬቱ ጭምር ቅድሚያ ክፍያ እየወሰደ ስራ ሲጀምር ደግሞ የተወሰነ ገንዘብ አምጡ ብሎ እየተቀበለ በሊዝ ከወሰደው አከባቢ በተጨማሪ የራሱ ያልሆነ መሬት መሸጥ ጀመረ። የኮንስትራክሽኑ ሥራ በማዝገሙ ገዢዎቹ መሬታችንን እንወቅ ብለው ጠየቁት። ለመሬቱ ቁጥር እየሰጠ ይሄ የአንተ ነው፣ ይሄ የእገሌ ነው እያለ ደልድሎ ስለነበር ሰዎቹ መሬቱን ለመረከብ ሲሞክሩ ከድርጅቱ ውጭ የማዘጋጃንና የግል ንብረቶችን ጭምር ሸጦ በመገኘቱ የኩባንያው ሥራ ቆመ። በተጨማሪም ግለሰቦች እነዚህ መሬቶች "እኔ የገበርኩበት፣ ይዞታውም የእኔ ስለመሆኑ በካርታዬ መሠረት መንግሥት ያረጋገጠልኝ" ነው በማለት ከጃክሮስ መሬት የገዙትን ሰዎች አስደነገጧቸው። መንግሥት ራሱ ሳይቀር "ይሄማ የመንግሥት መሬት ነው" በማለት ከግለሰብ ጋር ክርክር ገጠመ። ሰዎች ሁሉ ግራ ተጋቡ።

ይሄ ሁሉ ችግር እንዳይፈጠር ኢንጂነር ጌታቸው የቻሉትን ያህል ጃክሮስ ሥራውን በአግባቡ እንዲሰራ ሞክረዋል። በእሳቸው ሊስተካከሉ የሚችሉትን አስተካክለዋል።

ነገሩ ጥሩ አለመሆኑን ሲረዱ ይሄኔ ሥራ ለመልቀቅ ማሰላሰል ጀመሩ። ይህንን ሃሳብ እያወጡና እያወረዱ ባለበት ሰዓት የጃክሮስ ወንድምና ሌሎች ጥቂት የድርጅቱ የአክስዮን ባለድርሻዎች በየጊዜው ወደ እሳቸው እየመጡ የተለያዩ ምክንያት እያቀረቡ ገንዘብ እንዲሰጧቸው ይጠይቃሉ። ኢንጂነሩ ገንዘቡ የኩባንያው መሆኑን እያስረዱ፣ ከፈለጉ ሼራቸውን እየሸጡ ገንዘባቸውን

መውሰድ እንደሚችሉ፣ አለበለዚያ ግን የኩባንያውን ገንዘብ እንደማይሰጧቸው አስታወቋቸው። ይሄ ጭቅጭቅ ሲደጋገም ኢንጂነር ጌታቸውን ሰላም ነሳቸው። ስለዚህ ሥራውን የመልቀቅ ውሳኔ ላይ ተቃረቡ።

ሥራውን ከመልቀቃቸው በፊት እሳቸውን ብለው ወደ ኩባንያው ለተጠጉ ሰዎች ምክራቸውን ለግሰዋል። "ቦታውን የወሰዳችሁት በአነስተኛ ዋጋ ነው፣ ቦታው ከእጃችሁ ከወጣ ትከስራላችሁ። ስለዚህ የቦታውን ሁኔታ ህግ በሚፈቅደው መልኩ ከማዘጋጃ ቤት ጋር ጨርሱና መሬቱን ተረከቡ ያልተከፈለውን የሊዝ ዋጋ ብትከፍሉ አትጎዱም" ብለው ምክራቸውን ሰጡ። ብዙዎቹም የያዙትን ቦታ በህግ የራሳቸው ለማድረግ ችለዋል። በመጨረሻም ኢንጂነር ሥራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቃቸውን አሳወቁ።





# ምዕራፍ አሥራ ሶስት

## የጌት ኮንሰልታንሲ መቋቋም

ኢንጂነር ጌታቸው ከጃክሮስ ሥራቸውን በለቀቁበት ወቅት ሁሉም ነገር የመንግስት እየሆነና የመንግስት ቁጥጥሩ ከፍተኛ ስለሆነ ቦታውን ፕላኒንግና በላንድ ስኬፕ አርኪቴክቸር "ጌት ኮንሰልታንሲ" የሚባል የኮንሰልታንሲ ድርጅት በማቋቋም መንቀሳቀስ ጀመሩ።



**የኢንጂነር ጌታቸው የግል መሥሪያ ቤት ቢሮ (ጌት ኮንሰልታንሲ)**

ከንግሥት ሥራቸውን ሊሠሩ የሚችሉበትን ቦታ ጠየቁ። ከነገ

ዛሬ እየተባለ እሺም እምቢም የሚል በቦታው ጠፋ። የእሳቸው የሆነ ከአባታቸው ለጎጆ መውጫ የተሰጣቸው መስቀል አደባባይ አጠገብ አንድ ቦታ ነበራቸው። ቦታው በመንግሥት አልተወሰደም፣ ግብርም እየገበሩበት ነበር።

"የራሴ የሆነውን ቦታ ሥጡኝ፣ ወይ ደግሞ ይሄ ቦታ መሃል ከተማ ነው ካላችሁ በምትኩ ሌላ ቦታ ይሰጠኝ" በማለት ለማዘጋጃ ቤት ጥያቄ አቀረቡ። "ቦታውን የምፈልገው በአገሪቱ የሌለ እጅግ ጠቃሚ የሆነ የላንድስኬፕ ትምህርትን ለማስተማር የሚያስችለኝ ትምህርት ቤት ለማቋቋም ነው" በማለት ነበር የቦታ ጥያቄያቸውን ያቀረቡት። በጊዜው የከተማው ከንቲባ የነበሩት ከንቲባ ግዛው" በሶስት ቀን ውስጥ መልስ እንዲሰጠኝ አዘዙ ተፈፃሚ ባለመሆኑ ሌላም አስቸኳይ ትዕዛዝ ከሰጡ በኋላ ለም ሆቴል ከመድረሳችን በፊት በስተቀኝ በኩል የሚገኘውን መሬት መውሰድ ይችላል" ብለው ፈቀዱ።


ግን ቦታው ከፍተኛ የኤሌክትሪክ የሃይል መሥመር የተዘረጋበት ስለሆነ ችግር እንዳይፈጠር የሚል ውዥንብር ተፈጠረ። መሥመሩ የተዘረጋው ከዩጎዝላቪያ በመጡ ኤክስፐርቶች ሲሆን፣ በጊዜው ኢንጂነር እራሳቸው ማዘጋጃ ቤት ውስጥ ነበር የሚ ሰሩት። "ቦታው ላይ 30 ሜትር ያህል ሪዘርቭ ተደርጓል" የሚል ነበር ክርክሩ። ግን ይሄ ግምት ትክክል አይደለም ይላሉ ኢንጂነር ጌታቸው። "የተከለለው 16 ሜትር ብቻ ነው። ወደ ግምባር 8 ሜትር፣ ወደ ጎን 8 ሜትር ነው። ከዛ ውጭ ግን ያለው ቦታ ሥራ ላይ መዋል ይችላል፣ በሚል የመብራት ኃይል ባለስልጣን ጥናቱን ካየ በኋላ መስራት ይችላል ተባለና ተወሰነ።

እዚህ ውሳኔ ላይ ከተደረሰ በኋላ፣ "ውሳኔውን ቱሪዝም ይደግፈዋል ወይ?" የሚል ጥያቄ በመነሳቱ ጥያቄውን ለቱሪዝም አቀረብኩ። ቱሪዝም የራሱን ጥናት አካሄደና "ውሳኔው በጣም የሚደገፍ ነው" ሲል መልስ ሰጠበት።





ይሄ ሁሉ ውጣ ውረድ ከታለፈ በኋላ፣ አንዱ ባለሥልጣን አንድ ሲል፣ ሌላው ደግሞ ሌላ ሲል ጊዜው ከልክ በላይ ተጎተተ። ትንሽ የሙስና ነገሮች ከወዲህና ከወዲያ ብልጭ ድርግም ማለት ጀመሩ።


የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር
MINISTRY OF WORKS AND URBAN DEVELOPMENT

This is to Certify that

Getachew Mahtemeselasie

is registered as

Practicing Landscape Arch

in accordance With the Powers and duties vested in Ministry of Works and Urban Development by Establishment Proclamation no. 41/85 article 9

In witness whereof the Seal of the Ministry is hereto affixed.

GIRMA ABEBE
Contract Administration
Registrar Supervision and Regulation
Dep't Head

Chief engineer
Ministry of Works and Urban Development

Registration No. PLA00 Date OCT. 1995

This Certificate is held subject to the provisions of the Guidelines for the registration of Professionals and Consultants

ይሄኔ አንድ ነገር መወሰንና ሥራውን መጀመር አለብኝ በሚል ኢንጂነር ቢሮውን ብቻ በተከራዩት ቤት ውስጥ አቋቋሙ። መስቀል አደባባይ፣ አንበሳ ህንፃ ላይ ከተከራዩት ቢሮ ውስጥ ሥራቸውን ጀመሩ። ባለሙያዎችም ቀጠሩ። ሙያው አዲስ ስለሆነ የሚሰሩትን የስራ ዝርዝር ለኤምባሲዎች፣ ለናዝሬት ቴክኒካል ኮሌጅ እና ለበርካታ ግለሰቦች አስታወቁ።

የላንድስኬፕ ሥራው በግለሰብ ዘንድ ደህና ተቀባይነት ሲያገኝ በጊዜው በነበሩ አንዳንድ የተመሰቃቀሉ ሁኔታዎች ስራቸውን ለመስራት አላስቻላቸውም። ጨረታ ለመሳተፍ በሚሞክሩበት ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ውስጥ ለውስጥ በሚፈጥሩዋቸው ግንኙነቶች ሞያቸው ያልሆኑ የምህንድስና ባለሞያዎችና ድርጅቶች ስራዎቹን ይወስዱባቸዋል። "እኛ ይህን ሥራ አግኝተናል። አንተ ከእኛ ጋር እንደምትሠራ አስመስለህ የሥራና የትምህርት ደረጃህን የሚገልጽ (ሲቪ) ስጠንና እንጠቀምበት" ለዚህም የተወሰነ እንከፍላለን በማለት ይጠይቋቸዋል።

"እናንተ የእኔን የሥራ ልምድና የትምህርት ደረጃ ማስረጃ አቅርባችሁ፣ ጨረታውን አሸንፋችሁ። ግን ሥራውን ማነው የሚሰራው?" የሚል ጥያቄ ኢንጂነር አነሱ። የተድበሰበሰ መልስ ተሰጣቸው። ኢንጂነር በተሰጣቸው መልስ አልረኩም። "ይሄ የውበት ጥያቄ ነው። እናንተ ደግሞ ችሎታው የላችሁም" ሥራው ቢበላሽ የሚጎድፈው ስም የእኔ ነው የሚል መልስ ይሰጧቸዋል። "ስሜንና ሙያዬን ያጎድፋል" በማለት ለመተባበር ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ይገልፃሉ።

በዛ ላይ 1500 ብር የነበረው የቤት ኪራይ በአንድ ጊዜ ወደ 3700 ብር ገባ።ታክስ አለ። ለሠራተኛ የሚከፈለው ገንዘብ በራሱ አለገቢ






መሸፈን የሚቻል አልሆነም። ለሲቪል ኢንጂነሩ፣ ለአርክቴክቱ፣ ለድራፍት ማኑና ለሌሎች ቴክኒሺያኖች የሚከፍሉት ገንዘብ በጣም ከባድ ሆኖ አገኙት።የስራውን አጠቃላይ ክብደት ሲገልጹት ኢንጂነሩ የሚከተለውን ብለዋል፦ "እንዲህ ዓይነቱን ሥራ በግል ይቅርና እራሱ ማዘጋጃ ቤቱም ሥርዓት ያለው ቢሮ አቋቁሞ ሥራውን ለማንቀሳቀስ ብዙ ፈተናዎች ሊገጥሙት ይችላል"

ስለዚህም ቢሯቸውን ዘጉት። በመሰረቱ ዋናው ትኩረታቸው ሙያው በትምህርት ቤት ደረጃ እንዲሰጥና እንዲስፋፋ ለማድረግ ትምህርት ቤት ማቋቋም ነበር። ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ትምህርቱን ከኢለመንተሪ ጀምሮ በማስፋፋት እስከ ኮሌጅ ደረጃ ለማድረግ ነበር ዕቅዳቸው፤ ይሁንና አልተሳካላቸውም። ስለዚህም "የጌት ኮንሰልታንሲ" ቢሯቸውን ዘጉ።

# ምዕራፍ አሥራ አራት

## ቤተሰባዊ ጉዳይ

ኢንጂነር ጌታቸው ከጀርመን ሃገር ተመልሰው ሥራ ቢይዙም መጀመሪያ ላይ ይኖሩ የነበሩት በእናት በአባታቸው ቤት ውስጥ ነበር፡፡



ኢንጂነር ጌታቸው ከእህታቸው ከወ/ሮ ሐረገወይን ማህተመሥላሴ ጋር

አንድ ሰው ትዳር ለመያዝ የራሱ ቤትና መተዳደሪያ የግድ ያስፈልገዋል፡፡ እሳቸው አሁን ማዘጋጃ ቤት ውስጥ በሙያቸው





ተቀጥረው የራሳቸውን ገቢ ማግኘት ችለዋል፡፡ መተዳደሪያ አገኙ ማለት ነው፡፡ አሁን ጎጆዋን መቀለስ ብቻ ነበር የቀራቸው፡፡

ለእሱም አልሰነፉም፡፡ እናታቸው ቀበና አከባቢ በሰጧቸው መሬት ላይ በቅርፁም በይዘቱም ውብ የሆነ ቤት ሰሩ፡፡ ኢንጂነሩ ለቤታቸው ውበት ለመፍጠር ሙያቸው ቅርብ ነበረና በሠሩት ግሩም የሆነ ቤት ያልተገረመ አልነበረም፡፡

ቤታቸውን ውብ አድርገው ከሰሩ በኂላ የተለያዩ የቤት እቃዎችን መገዛዛት ጀመሩ፡፡ እቃዎቹን በአብዛኛው ከውጭ ሃገር ዜጎች ላይ ገዙ፡፡ አሁን ቤቱ እየተሟላ ሲሄድ የኑሮ አጋር፣ ሚስት ፍለጋ መጣ፡፡

ዘመድም ጓደኛም ይቺን አግባ፣ ያቺን አግባ እያሉ ይወተውቷቸው ጀመር፡፡ እሳቸውም በግብዣውም፣ በቤተሰብ ውስጥም በተለያየ ግብዣዎችም ላይ ዓይናቸውና ልባቸው የሚያርፍባት ሚስት ሲፈልጉ ቆዩ፡፡

ዞሮ ዞሮ የእህል ውሃ ነገር አንዷን ነውና የሚያጋጥመው፣ ልባቸው ወ/ሮ የሺሃረግ ዋዠጎ ላይ አረፈ፡፡ ወ/ሮ የሺሃረግ ዋዠጎን በመልክም፣ በባህሪም እንዲሁም በትምህርት መልካም ሆነው ስላገኟቸው ትዳራቸውን ከእሳቸው ጋር መሠረቱ፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው ሥራ ውለው ሲመጡ ሰላም አግኝተው አረፍ የሚሉበትን ትዳር ጀመሩ፡፡ ሁለት ልጆችም ወለዱ፡፡ የመጀመሪያ ልጃቸው ወንድ ሲሆን ኢንጅነር ክፈተው ጌታቸው ይባላል፡፡ ሁለተኛዋ ልጃቸው በልዩ ጌታቸው ትባላለች፡፡ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ቢ.ኤስ.ሲ. አላት፡፡

ትዳሩ እንዲህ ባማረና በሠመረበት ሰዓት ልጆችም ትምህርታቸውን

ከኤለመንተሪ ጀምሮ ወደ ላይ በከፍተኛ ውጤት እያደጉ ባለበት ሰዓት የብዙ ቤተሰቦችን ሰላምና ኑሮ ያመሰቃቀለው ደርግ የመንግስት ሥልጣን ጨበጠ። ከዛን ጊዜም ጀምሮ የኢንጂነር ጌታቸው ቤትና ቤተሰብ ለመከራና ለእንግልት ተዳረገ።

ኢንጂነሩ ታሠሩ፣ ማጣት መጣ፣ መከራ በዓይነት በዓይነቱ በቤተሰቡ ላይ እንደ ዶፍ ወረደ። ቤቱ ቀደም ብሎ ተሽጦ ቤት ተከራይተው የሚኖሩት ሚስትና ልጅ ከተከራዩበት ቤት እንዲባረሩ ተደረገ። ሚስት ለወራት ታሥረው ተፈቱ።

እግዚአብሔር የራሱ መንገድ አለውና የኢንጂነር ጌታቸውን ልጆች በወንድማቸው በአቶ ሰለሞን ማህተመሥላሴ አማካይነት ታደጋቸው። የኢንጂነር ጌታቸው ወንድም አቶ ሰለሞን ማህተመሥላሴ መጀመሪያ እራሱ ከዚህ ሃገር ከነበረው ወቅታዊ ችግር አመለጠ።

የዓለማያ የእርሻ ኮሌጅ ምሩቅ የነበረው አቶ ሰለሞን በደርግ ከፍተኛ ክትትል ይደረግበት የነበረ ቢሆንም በዘዴ ከሃገር ለመውጣት ችሏል።

መጀመሪያ እንደሚዝናና ሰው መስሎ ወደ ሶደሬ በመሄድ የመኝታ ክፍል ይይዛል። ይከታተሉት የነበሩት የደህንነት ሰዎች አቶ ሰለሞን ክፍል መያዙን ሲያረጋግጡ "አገር ሰላም ነው፣ ክፍል ይዟል የትም አይሄድም" ብለው ዘና ሲሉ ሆቴል ውስጥ ያለ ለመምሰል እቃ ትቶ እሱ በመኪናው ሃገር አቋርጦ ኬንያ ገባ። ከዛም ወደ አሜሪካ አቀና።

አቶ ሰለሞን በአሜሪካ ሃገር ውስጥ የኢትዮጵያን ቡና በማስተዋወቅ ከፍተኛ ድርሻ አለው። የቡናውን የአቆላል ሥርዓትና ጣዕሙ በሰፊው እንዲታወቅ አድርጓል። ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረበትም ጊዜ የቡና ማበጠሪያና ማሽጊያ መሣሪያዎችን ያስተከለ የቴክኒክ ሰው ነው። በመሠረቱ ከአለማያ የእርሻ ኮሌጅ የቀሰመውን ትምህርት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሙያ ጓደኞቹ ጋር የተገበረ ባለሙያ ነበር።





አቶ ሰለሞን አሜሪካ ገብቶ እራሱን እንዳደላደለ በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ አሁን በእሱ ሥም የሚጠራውን የኢንጂነር ጌታቸውን ወንድ ልጅ ክፌተው ሰለሞንና የእሱ ታናሽ የሆነችውን በልዩ ጌታቸውን ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ ማሻገር ነበር። እንዳሰበው አልቀረም አሻገራቸው፣ ትምህርታቸውንም እንዲቀጥሉ ሁሉን ነገር አመቻቸላቸው።

በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ማስተርሱን የያዘው ኢንጂነር ክፌተው በአሁኑ ጊዜ በዴል ኮምፒውተር ኩባንያ ውስጥ አሉ ከሚባሉት ሃላፊዎች አንዱ ለመሆን በቅቷል። መጀመሪያ በታይዋን የሚገኘው የዴል ዲዛይን ሴንተር ማዕከል ማኔጂንግ ዳይሬክተር ነበር። በአሁን ጊዜ ደረጃውን አሳድጎ ህንድና ቻይናን ጨምሮ ለሰባት የእስያ ሃገሮች የዴል ኮምፒውተር ኩባንያ ተጠሪ ሆኖ ይሰራል። ትዳርም መስርቷል። ያገባው የሃኪሙን የታዋቂውን የፕሮፌሰር ታይንን ልጅ ነው።

ሴት ልጃቸው ወ/ት በልዩ ጌታቸውም በአድምኒስትሬሽን ማስተርሷን ለመያዝ ጥቂት የትምህርት ዓይነቶች ቀርቷታል። በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ ሃገር የመንግሥት ተቀጣሪ ሆና ትሰራለች።

ደርግ በትዳራቸው ላይ የሰነዘረውን ሰይጣናዊ በትር አስመልክተው ኢንጂነሩ ሲገልፁ፡- "ደርግ እኔን ከበደለኝ በደሎች ሁሉ የከፋ ነው የምለው ከባለቤቴ ጋር የነበረኝን ግንኙነት እንዲቋረጥ ያደረገው ነው። አሁን እስዋ ለእኔ እንደ እህቴ ናት። እሷም አላገባችም፣ እኔም አላገባሁም። በደርግ ምክንያት ነው ቤቴ የፈረሰው" ብለዋል።

# በጃንሆይ ላይ የኢንጂነር ጌታቸው አስተያየት

ኢንጂነር ጌታቸው ለግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ እጅግም ቅርብ አለመሆናቸውን ቢገልፁም ከእሳቸው ጋር በፈጠሩት የሥራ ግንኙነት ብዙ መገንዘባቸውን ይናገራሉ። ጃንሆይ አርቆ አስተዋይ ስለመሆናቸው፣ ነገሮችን በፍጥነት የመረዳት ችሎታ እንዳላቸው፣ ጥያቄያቸው አጭር፣ መልሳቸውም እጥር ምጥን ያለ ስለመሆኑ ማስተዋላቸውን በአድናቆት ይገልፃሉ። በተለይ ሰው የማይንቁና ወጣቱን ምሁር ወደ እሳቸው ለማቅረብ የነበራቸው ፍላጎትና ቀናነት በጣም ጎልቶ በማስተዋላቸው ይህ ባህሪይ ወደ እሳቸው እንዲሳቡ እንዳደረጋቸው ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

ጃንሆይ ይሄን ፍጠር፣ ይሄን ውሰድ የሚሉ መሪ ሳይሆኑ "ይሄን ነገር እንዴት ታየዋለህ?" የሚል ጥያቄ እንደሚያዘወትሩና መልሶቻቸው "መልካም ነው" ይሁን፣ "ጥሩ ነው"፣ "በዚህ ቀጥል" የሚሉ ሆኖ የንግግራቸው ማሳረጊያ "እግዚአብሔር ይባርክህ" የሚል እንደነበር ኢንጂነር ጌታቸው በአክብሮት ይገልፃሉ።

አንድ ሁለት ግዜ እንዲሁም አልፎ አልፎ ሰዎች በስህተትና ብዙም ባልተረዱት ነገር ጃንሆይ ዘንድ ከሰዋቸው ቀርበው እንደነበረ የሚያስታውሱት ኢንጂነር ጌታቸው በተለይ በበቃ ጉዳይ በተከሰሱበት ክስ የሚያስታውሱት አላቸው፡- ክሱ "ጌታቸው ትዕዛዙን አልተቀበለም" የሚል ነበር። ጃንሆይ "አሁን አንተ እዛ ሄደህ ትሠራዋለህ?" ብለው ኢንጂነር ጌታቸውን በቁጣ መልክ ይጠይቃሉ። ኢንጂነር ጌታቸው ሁኔታውን ዘርዘር አድርገው ያስረዳሉ፡- "ግርማዊ ሆይ ነገሩ እንደእሱ አይደለም። ቡናውን





ለ30 ዓመት ተጠቀሙበት። አሁን እንደገና ለ30 ዓመት ኮንትራቱ ይታደስልን ነው የሚሉት። ለ30 ዓመት ኮንትራቱ ከታደሰላቸው የሚመረተው ቡና ሳይሆን እንጨት ብቻ ነው የሚሆነው፣ ከ60 ዓመት በኋላ በቦታው ያሉ መኪናዎቹም ቤቶቹም ያረጃሉ። ባይሆን ለምን እንዲሁ ይሰጠን ብለው በምስጋና አይወስዱም" የሚል መልስ ይሰጣሉ።

"እንዲህ ነው ነገሩ" ይላሉ ጃንሆይ። ከዛ ለክስ አቅራቢዎቹ "በሉ ከእሱ ጋር ተነጋገሩና ጨርሱ" የሚል መልስ ሰጥተዋል።

የጃንሆይን ቀልብ ለመሳብ ሶስት ቡድኖች ይሻኮቱ የነበረበትን ሁኔታም ሲገልጹ የሚከተለውን ብለዋል፡- "እርስ በርስ የሚሻኮቱ ሶስት ቡድኖች ነበሩ። አንደኛው ንጉሳውያን ቤተሰብ እራሱ አለ፣ ወጣቱ ምሁር አለ፣ ሌላው ቀደም ብሎ ያገለገለው ቡድን አለ። ሁሉም የራሱን የሥልጣን ትግል ያደርጋል። እነዚህን ቡድኖች በአንድ አድርጎ ማስተባበር ሸክሙ የጃንሆይ ነበር።"

ኢንጂነር ጌታቸው የተከፉበትን ጊዜ ሲያስታውሱ በሥራ ዓለም ውስጥ መከፋት ያጋጥማል ነገር ግን ምንም ቢሆን በደርግ በታሰሩበት ወቅት የአባታቸው ሕክምና አጥቶ መሞት ከሁሉም የከፋ እንደነበር ነው የሚገልጹት። ያም ሆኖ ግን አላዋቂዎች ያደረሱብኝ በደል ነው ብለው ስለሚያምኑ መከራውን በህይወታቸው ውስጥ ቦታ አልሰጡትም።

"ለሥልጣን፣ ለገንዘብና ለሐብት ግድ የለኝም። ዓላማ አለኝ። የሚያስደስተኝ ነገር ዓላማዬን አቅጄ ያ ዓላማ ውጤት ላይ ሲደርስ ማየት ነው። ይሄ ነው የእኔ እርካታ በዚህ መልኩ የተሳኩልኝ

ሥራዎች አሉ። በእነዚህ ሥራዎቼ እኔ ብቻ ሳልሆን አባቴም በእኔ ሥራ መደሰታቸውንና ሥሜን የሚያስጠራ ልጅ ነው መባሌን በጣም አድርጌ አከብረዋለሁ።" ብለዋል በሕይወታቸው ስለሚደሰቱበት ነገር ሲገልጹ።

ኢንጂነር ጌታቸው ለህይወታቸው አንድ አብይ መርህ አላቸው። ይህን መርህ በኑርዋቸውም ሆነ በሥራቸው በተግባር ማዋላቸውን በልበ ሙሉነት ይገልፁታል እሱም "እውነት!" ነው። "ኢትዮጵያን ለማዳንና ታላቅነቷን ለማስረገጥ መዘውሩ ለእውነት መቆም ነው" ካሉ በኋላ "እረ ጅም ንግግር የሚያስፈልግ አይመስለኝም! ሁሉም ሰው ያውቀዋል። ኢትዮጵያን ከርሃብ፣ ከችግር፣ ከውርደት ማውጣት የሚቻለው አንድ ነገር ሲኖር ነው። ይሄውም እውነት ሲኖር ብቻ ነው!" በማለት ገልፀዋል።





# ምዕራፍ አስራ አምስት
# የተሰጡ ነፃ አገልግሎቶች

ኢንጂነር ጌታቸው ማህተመሥላሴ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰጡት አገልግሎት ከ-እስከ ተብሎ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም።



በመሃንዲስነት ያሰሩት የቅ/ሥላሴ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

በመሠረቱ ኢንጂነር ጌታቸው በሕይወት ዘመናቸው ከቤተ-ክርስቲያ ኒቱ የተለዩበት አንድም ግዜ እንደ ሌለ ሙሉ የሕይወት ታሪካቸው በራሱ የሚመሰክረው ነው። የወላጅ አባታቸውንም

ምክር ከዳር አድርሰው ምሳሌነታቸውንም ተግባራዊ አድርገዋል። የአባታቸውን አርአያነትም ሲገልጹ የሚከተለውን ብለዋል፦ "አንድ ሰው በተመደበበት ሥራ ላይ ለተገልጋዩ ጥሩ አገልግሎት ቢሰጥ ይመሰገናል፣ ክብርና ሞገስ ያገኛል፣ ለታላቅ ኃላፊነት ይመረጣል፣ ከሥጋት ነፃ የሆነ ኑሮ ይኖራል፣ እግዚአብሔርም በላቡ ያገኘውን ሃብት ይባርክለታል፣ በችግሩም ግዜ ከጎኑ ይቆምለታል፣ ከህሊና ወቀሳም ይድናል፣ የወለደውም ይባረካል፣ ይኸውም ለፈጣሪህ ጭምር ስታገለግል ነው" እያሉ አባቴ ክቡር ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ ወ/መስቀል ይመክሩኝ ነበር። ምክራቸውም በተግባር የተደገፈ ስለመሆኑ ለቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ-ክርስቲያን፣ ለእቲሳ ተክለሃይማኖትና ለሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ያደርጉ የነበሩት ስጦታና አገልግሎት ምስክሮች ናቸው። እኔም በእንዲህ ዓይነቱ ተግባር የእሳቸውን አርአያ እንድከተል ገፋፍቶኛል። ስሠራባቸው ከነበሩ መሥሪያቤቶችና በግል የማውቃቸውን ሰዎች በማስተባበር፣ እኔም አቅሜ የሚፈቅደውን አውጥቼ ለቤተ-ክርስቲያናቱ አንቱ የተባሉ ሥራዎችን ሠርቻለሁ።"

ኢንጂነሩ በአብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ ከሠርዋቸው በርካታ ሥራዎች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፦

ሀ) መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ

1. በደርግ ዘመን ሃይማኖት አደጋ ላይ በወደቀበት ወቅት ቤተ ክርስቲያኖችን ተጠግተው የሚኖሩ መነኮሳት ጭምር በተራቡና በታረዙ ሰዓት ኢንጂነሩ በግዜው ከሚሠሩበት የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች አስተዳደር፣ ለስደተኞች ተብሎ ከመጣው ተራፊ እህል እየለመኑ፣ ለምሳሌ ለመናገሻ ቅዱስ





ጊዮርጊስ (አራዳ) ቤተ-ክርስቲያን ሁለት ሺ (2,000) ኩንታል ፋርኖ ዱቄት፣ ዘይትና አልባሳት እንዲገኝ አድርገዋል።

2. አዳራሹ፣ ሙዚየሙና የመቃብር ፋካዎችም የተሰሩት ለነዳያንና ለካህኑ እህሉ በአነስተኛ ገንዘብ ከተሸጠ በኋላ በተገኘ ገንዘብ ነው።
3. አሁን ለኪራይ የተሰሩት በርካታ ቤቶች ከፊል የግንባታ ወጪ (ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ) ሲሆን ገንዘቡ የተገኘው ከመቃብር ፋካዎች ሽያጭ ነው።
4. ቤተ-ክርስቲያኑ ጣራው በማፍሰሱና ቤቱም እድሳት ስላስፈለገው ዘመድ ወዳጅ አስተባብረው በተገኘው ከ102,600 ብር በላይ በሆነ ገንዘብ እደሳውን አከናውነዋል።
5. በግቢው ውስጥ ያለውን የመኪና ማቆሚያ፣ ግቢው ውስጥም የእግረኛ መዘዋወሪያ አስፋልት ለማሠራት የሚያስፈልገውን ከ150,000 ሺ (አንድ መቶ ሃምሳ ሺ) ብር በላይ ቻይናውያኖችን በመለመን አሰርተዋል።
6. ሥራዎቹ ሲሰሩ ኢንጂነር ጌታቸው በልማት ኮሚቴ ውስጥ የቴክኒክ አማካሪ በመሆን አገልግለዋል።

ለ) በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ውስጥም ለቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ከሰጡት አገልግሎት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሰፊ አገልግሎት አበርክተዋል።

ሐ) በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ነፃ አገልግሎት የሰጡ ሲሆን ለምሳሌ፣

በቀጨኔ መድኃኒያለም፣ በቅዱስ ኡራኤል፣ በባዕታ ገዳም፣ በአዲስ ዓለም ገዳም፣ በደብረሊባኖስ ገዳም በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ

ኮሌጅ፣ እንዲሁም እቲሳ ተክለሃይማኖት ገዳም (አንድ ሺህ ኩንታል ፋርኖ ዱቄት በመስጠት) በቅርቡም የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ዕድሳትን በኃላፊነት በማስፈጸም በሙያቸው ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ነፃ አገልግሎቶችን አበርክተዋል። በማበርከትም ላይ ይገኛሉ። በተለይ በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ሕዝብ የሚፈወስበትን ጠበል ቤት በራሳቸው ገንዘብ ሠርተው ለቤተክርስቲያኑ አስረክበዋል።

ኢንጂነር ለቅድስት ቤተ-ክርስቲያንዋ በየሥራ ዘርፉ ላከናወኗቸው የምግባረ ሰናይ አገልግሎት በግንባር ቀደምትነት ተገኝተው ለፈፀሙትና ለሚፈጽሙት አገልግሎት የተግባር መዘክር ይሆን ዘንድ የማዕረግና የክብር መጠሪያ እንዲኖራቸው ሰላስፈለገ ቀደም ብሎ በትረ ሃይማኖት ከጥቅምት 20 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ "ሊቀ ትጉሃን ኢንጂነር ጌታቸው ማህተመ ስላሴ" ተብለው እንዲጠሩ በቅዱስ በፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስ ተፈቅዶላቸዋል።

ለቤተክርስቲያኒቷ የሰጧቸውን ነፃ የሙያ አገልግሎቶችን በተመለከተ ሁለት ባለሙያና መንፈሳዊ አባቶች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል እነሱም፡

1. የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የበላይ ኃላፊ ሊቀጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጢሞቲዎስ (የቅዱስ ሲኖዶስ አባል)
2. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህደ ቤተ ክርስቲያን የመንበረ ፓትሪያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ምክትል ሥ/አስኪያጅ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ አስተዳዳሪ፣ ምክትል ዲን ናቸው።

1. ብፁዕ አቡነ ጢሞቲዎስ

ኢንጂነር ጌታቸው ማህተመሥላሴ በተግባር ለቤተ ክርስቲያን





የሰጡትን አገልግሎት አስመልክተው በቅርቡ በአራት ኪሎ አካባቢ ለተሠራው ሕንፃ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በተመለከተ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መጽሔት ላይ ባስተላለፉት መልእክት የሚከተለው ይገኝበታል።

"መንፈሳዊ ኮሌጁ ያስገነባውን ሕንፃ ሥራ ከሚከታተሉት ሰዎች ዋነኛው ኢንጂነር ጌታቸው ነበሩ። በቅድሚያ በዲዛይኑ ሥራ ላይ አንዳንድ ክፍተቶች እንዳሉ ተገንዝበው አስፈላጊውን የማስተካከያ ሃሳብ በማቅረብ አሻሽለውታል። ካሻሻሉትም ውስጥ፡-

- የአገልግሎት መስጫ ክፍሎቹን በጣም የጠበቡትን ከፊትና ከኋላ ሊሠሩ ታቅደው የነበሩ በረንዳዎች ወደ አገልግሎት መስጫ ክፍልነት ቀይረው ተጨማሪ አገልግሎት እንድናገኝ አድርገዋል።
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተከራየው ሕንፃ ላይ ያለውን ጣራ ለመናፈሻነት እንዲውል ታይልስ እንዲነጠፍበት በማድረጋቸው ሥፍራው ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆን አድርገዋል።
- በዚህ ሕንፃ ላይ ኮኔክሽን ብሎክ በሚል ለሚታወቀው ክፍል እንደመተላለፍያ ታስበው ከነበሩት ሶስት ቢሮዎች አንዱ አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ መተላለፊያውን ወደ ባለ ሁለት ፎቅ ክፍልነት በመቀየር ተጨማሪ ቢሮዎች እንዲገኝ ረድተዋል።
- በመኖሪያ ሕንፃ ሥር ለመጋዘን ታቅዶ የነበረውን ሰፊ ቦታ ይዘቱን በመለወጥና በዘመናዊ ሁኔታ በማደራጀት ህንፃው ሁለገብ እንዲሆን አድርገዋል።
- በኮኔክሽን ብሎክ ላይ የሚገኙ ሶስት ክፍሎች ለቢሮ ታስበው በሮቻቸው ወደ ግቢው ውስጥ የነበረ ሲሆን ይህን ዲዛይን ቀይረው ከዋናው መንገድ ትይዩ እንዲሆን በማድረግ የተሻለ ይዘት እንዲኖረው አስችለዋል" በማለት ገልጸዋል።



**በጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በገንዘባቸውና በመሪነት ባሠሩት የጠበል ቤት ሲሸለሙ**

## 2. ንቡረእድ ኤልያስ አብርሃም

በመንፈሳዊ ትምህርት የቅኔ፣ የዜማ፣ የትርጓሜ መጽሐፍት ባለሙያና መምህር እንዲሁም በዘመናዊ ትምህርት በመጀመሪያ ድግሪ ያላቸው ንቡረእድ ኤልያስ የኢንጂነር ጌታቸውን አጠቃላይ ባህሪይ "የዘመናችን አብርሃም" ሲሉ በተከበረና በታላቅ ስም ጠርተዋቸዋል፡፡

ኢንጂነር ጌታቸውን የሚያውቋቸው በቤተክርስቲያን ልጅነታቸው መሆኑን የሚገልጹት ንቡረእድ ከኢንጅነሩ ጋር በመሆን ለበርካታ





ዓመታት በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በልማት ኮሚቴ አባልነት አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡

በእነዚህ ዓመታት በኢንጂነሩ የግል ባህሪይ በመደነቅና በማክበር ሲናገሩ፡ - "ሰለቸኝ፣ ደከመኝ የማይሉና በተፈጥሮዋቸው እረፍት የሚሹ ሆነው አላገኘኋቸውም፡፡ ያላቸው ትጋት፣ ተቆርቋሪነት፣ እውነት የምትባለዋ ነገር ምንም ሳትነካ፣ ቀጥ ብላ እንድትቀጥል የሚጥሩ ቅን አስተሳሰብ ያላቸው ሰው ናቸው፡፡" ብለዋል፡፡

አሁን ያለንበት ዘመን የሰው አመለካከት ከጥቅም ጋር በአብዛኛው የተያያዘ ቢሆንም፣ ኢንጂነር ጌታቸው ከዚህ አስተሳሰብ በፍፁም የፀዱ ናቸው ይላሉ ንቡረእዱ፡፡

በአንድ ወቅት ካቴድራሉ ዝናብ ያፈስ ነበርና ጥገና ያስፈልገዋል ተብሎ በካቴድራሉ ባለሥልጣን ሲወሰን፣ ኢንጂነር ጌታቸው በልማት ኮሚቴ ውስጥ ሆነው ሥራውን በጥብቅ ሲከታተሉ ያስተዋሉትን እስከአሁን ከህሊናቸው እንዳልጠፋ ነው ንቡረእድ የሚናገሩት፡፡ "የቤተ ክርስቲያኒቷን ንብረት ለመጠበቅ ሲሉ ያደርጉ የነበረው ጥረት እስከ ምን ግዜውም ይማይረሳ ነው" ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በመቀጠልም "ኢንጂነር ጌታቸው በተለያዩ ሰንካላ ሥጋዊ አስተሳሰቦች የሚበገሩ አይደሉም፡፡ ይሄ ደግሞ በአንድ ቤተክርስቲያን ብቻ አይደለም፡፡ በገነት ጽጌ፣ በቅዱስ ጊዮርጊስና በሌላም እኔ እስከማውቀው ድረስ ወደ 10 የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናት በእሳቸው ሙያ እየታገዙ እንደሚሰሩ ውስጤ ይሰማኛል፡፡

"እንደሳቸው ዓይነት ሰው በግል ማግኘት ቀርቶ ማየቱ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህን ሁሉ ሲያደርጉ አንድ ሳንቲም አይቀበሉም፡፡ ለመመላለሻቸው ለሚጠቀሙበት መኪናቸው ቤንዚንም ቢሆን ከራሳቸው ኪስ እንጂ ከማንም አይወስዱም ነበር፡፡ እንከን የለሽ የቤተ ክርስቲያን ልጅ ናቸው" ብለዋል፡፡

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

## በኢንጂነር ጌታቸው ስራዎችና አስተሳሰቦች ላይ ከስራ ባልደረቦቻቸው የተሰጡ አስተያየቶች

## ዶ/ር አሸናፊ ኃይሌ

ዶ/ር አሸናፊ ሃይሌ በህግ ትምህርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ታንዛንያ በሚገኘው ኮሌጅ በመከታተል የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። በመቀጠልም በአሜሪካ ሃገር በማኔጅመንት በፒ.ኤች.ዲ ተመርቀዋል።

መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ውስጥ (በኤን.ጂ.ኦ) ስራ በጀመሩበት ወቅት የቅርብ አለቃቸው ኢንጂነር ጌታቸው ነበሩ። በግዜው የቀይ መስቀል ኃላፊው ዶ/ር ዳዊት ዘውዴ ነበሩ። የስደተኛውን ጉዳይ በኃላፊነት የያዙት ኢንጂነር ጌታቸው ነበሩ።

ስራው የሚሰራው (UNHCR) ተቆጣጣሪነት እና በጀት አቅራቢነት ሲሆን፣ ቀይ መስቀል ደግሞ ስራውን ተግባራዊ በማድረግ ነው።

ከምስራቅ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ይገቡ የነበሩትን የሱማሊያ ስደተኞችን በተመለከተ የኢትዮጵያ ቀይመስቀል እና እርዳታ ማስተባበሪያ በጋራ ሆነው ሲሰሩ የሱዳንን ስደተኞች በተመለከተ ደግሞ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ኃላፊነቱን ወስዶ ዲማ ውስጥ ይሰራ ነበር። ኢንጂነር ጌታቸው ማህተመስላሴ በግዜው የUNHCR ዋና አስተባባሪ ሆነው በሚሰሩበት ግዜ፤ ዶ/ር አሸናፊ ደግሞ የሉጂስቲክ መምሪያ ሃላፊ ሆነው ይሰሩ ነበር።

ዶ/ር አሸናፊ ስለ ኢንጂነር ጌታቸው መልካምነትና ከፍተኛ የስራ ብቃት ያላቸው ባለሙያ ስለመሆናቸው ቀደም ብለው የሰሙት ነገር ነበር።



በሳንደስኬፕ አርክቴክት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ

"ግን" ይላሉ፣ ዶ/ር አሸናፊ "አቶ ጌታቸውን ስመለከት አዲስ ስርአት ነው የተመለከትኩት። አሁን ለደረስኩበት ደረጃ መነሻ ምክኒያቴ እሳቸው ናቸው እላለሁ።"

"በዛን ግዜ በእሳቸው ስር አንድ አምስት የምንሆን ኃላፊዎች ነበርን። ያ ቡድን ከአሳቸው ጋር ከእድሜ አንፃር ሲታይ የ15 አመት የእድሜ ልዩነት ይኖረዋል የሚል ግምት አለኝ። ግን እሳቸው ይሄን ቡድን በዋናነት ይዘው አንድን አላማ ለማሳካት ያደርጉት የነበረውን ጥረት ስመለከት ኢንጂነር ጌታቸው ምሉእ የሆኑ ሰው መሆናቸውን ተረድቼያለሁ። ከጠዋት ጀምሮ እስከ ማታ የሚሰራውን ስራ ድቅቅ አድርገው ነው የሚሰሩት። ስራቸውን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ሲሰሩም መጪውን ጊዜ በማስተዋል ነው።"

"ለምሳሌ አንድ ጊዜ የሆነ ነገር ከማትያስ ጋር (አቶ ማትያስ በአሁኑ ጊዜ ዩጋንዳ ውስጥ የአንድ ኤን.ጂ.ኦ ካንትሪ ዳይሬክተር ናቸው።) አንድ ጥናት አዘጋጁ ይሉናል። እናም በታዘዝነው መሰረት ጥናቱን አዘጋጅተን እናቀርባለን። አቶ ጌታቸው የቀረበላቸውን ተመልክተው አርመው ወደ እኛው ይመልሱታል። እኛም እሺ እንልና እሳቸው ባረሙት መሰረት አስተካክለን እናቀርባለን። አሁንም አርመው መለሱት። አሁንም በታረመው መሰረት ተሰራና ቀረበላቸው። ስራው ተደጋግሞ በመመላለሱ እሳቸውን ማማት ጀመርን። እኚህ ሰውዬ ምንድን ነው የሚፈልጉት አልን። ለአምስትኛ ግዜ እንደገና ይታረም ብለው ሲመልሱልን እኔ ለማት ያስ ድራፍቱን (ረቂቁን) ኢንጂነር ጌታቸው የጣሉት አይመስለኝም። አሁን የተሰራውንና የታረመውን ሳየው ነገርየው ወደ ቀድሞው ወደ መጀመሪያው ተመልሷል። ስለዚህ እኔ እናገራቸዋለሁ እለዋለሁ። እሱ አይሆንም ተው ይለኛል። በመጨረሻ ተያይዘን ወደ ቢሮአቸው ሄድን። በመሰረቱ ሁለት የተለያዩ ነገሮችን በአንድ ላይ ማግኘት ከባድ ነው። ግን ኢንጂነር ጌታቸው ሁለቱን

አንድ ላይ የያዙ ሰው ናቸው። አለቃና አባት አንድ ሆነው ማለት ነው። ቢሯቸው ገባንና ‹ይህ ነገር እንዴት ነው?› ብለን በመጠየቅ እኔ የተሰማኝን አስረዳሁ። በጥሞና አዳመጡኝ ከዚያም ‹አያችሁ› የአንድ ሰው ሥም ጠቅሰው ‹ነገሩ ተጣጥሮ መንገስ ላይ ነው› ካሉ በኋላ እስቲ ተቀመጡና እንነጋገርበት አሉ።

“በመቀጠል አያችሁ እናንተ ወረቀቱ ከዚህ የሚወጣበትን ብቻ ነው የምታስቡት። እኔ እያሰብኩ ያለሁት ከዚህ ጽፌን ከሰደድን በኋላ UNHCR የፃፍነውን ጽሑፍ አንብቦ የሚመልሰውን መልስ ነው። ከዛ ደግሞ እነሱ ሲመልሱ፣ እኛ ደግሞ ለዛ መልስ የምንመልሰውን … ስለዚህ ከአሁን በኋላ ለአራት ግዜ የመላለስነውን ጽሑፍ ያ እዛ ያለ ሰው አራት ግዜ ሊያስብ ካልቻለ ጉዳዩ ያለቀ ነው የሚሆነው ማለት ነው” አሉን።

“ኢንጂነር ጌታቸው” ይላሉ ዶ/ር አሸናፊ የኢንጂነር ጌታቸውን ትካዜዎች በማስታወስ “በአንዳንድ ጉዳይ ከሰዎች ጋር የሚጋጩበት ግዜ አለ። የግጭቱ መንስኤ የእሳቸው ስህተት ሆኖ አይደለም። አዲስ ነገር ይታሰብና ለራስ ይሁን፣ ለሃገር ይሁን፣ ለምን ይሁን ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ሲፈጠር ከፍተኛ ሃዘን ይሰማቸዋል። ከዛ ይቺ ሃገር በኋላ ምን ልትሆን ነው? እንዴትስ ነው ሥራ ሊሠራ የሚች ለው? ብለው በመጠየቅ ከራሳቸው ጋር የሚነጋገሩ ይመስላሉ። ሁሉንም የድርጅቱን ፕሮግራም ከሃገራቸው የወደፊት እጣ ፈንታ ጋር ነው የሚያያይዙት፡ ፡” ሲሉ ይገልፃሉ።

ዶ/ር አሸናፊ ከኢንጂነር ጌታቸው ጋር ሲተዋወቁ ዕድሜያቸው ገና ወደ ሃያዎች መጨረሻ አከባቢ ነበር። ያንን ግዜ እንዲህ ሲሉ ያስታውሱታል፡ - “በዛ ዕድሜ ላይ እሳቸውን ማግኘቴ ዛሬ አሁን ለደረስኩበት ደረጃና ህይወት ትልቅ ትምህርት ቤቴ ነበር” ብለዋል።

ዶ/ር አሸናፊ ስለ ኢንጂነር ጌታቸው የሥራ ዲሲፒሊን ሲናገሩ፡-





“እሳቸው ዘንድ የሚታሰብ የእረፍት ቀን ብሎ ነገር የለም። ዛሬ እኮ እሁድ ነው ስትላቸው፣ እሁድ ስደተኛው አይበላም ያለህ ማን ነው? ይሉሃል። ወይ ደግሞ ዛሬ እኮ ፋሲካ ነው ሲባሉ፣ ስደተኛው ፋሲካ የለውም? ብለው አጣብቂኝ ውስጥ ይከቱሃል” በማለት ይገልፁታል።

ዶ/ር አሸናፊ ሃይሌ በሩዋንዳ የዘርማጥፋት ጭፍጨፋ በተካሄደበት ግዜ እሳቸው ለስደተኞች በሚሰጠው ዓለም አቀፋዊ ድጋፍ ውስጥ የሃገሩ ተጠሪ ሆነው ሰርተዋል። እንደዚሁም በሴንትራል አፍሪካ (ለ13 ሀገሮች) በስደተኞች ዙሪያ ለሚሠራው ሥራ ኮኦርዲነተር ነበሩ። በአፍጋኒስታንም ተመሳሳይ ሥራዎችን ሠርተዋል። በእነዚህ በሠሩባቸው ሥራዎች ሁሉ ከኢንጂነር ጌታቸው ጋር እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ያሳለፏቸውንና በኢንጂነር ጌታቸው ስሜት ላይ ያስተውሉት የነበረው ጭንቀት ሁሌም በየሥራ ቦታዎቻቸው ትዝ እንደሚላቸው ይናገራሉ። በእነዚህ ጭንቀትን ካዘሉ ትዝታዎች በተለየ ሁኔታ አንድ የሚያስታውሱት ልዩ አጋጣሚ አላቸው። ይህንንም ሲገልጹ፡-

“ያኔ ከአንዱ ወደ ሌላ ቦታ ለመገናኘት የምንጠቀመው በሬዲዮ ነበር። በወቅቱ ከአንድ የስደተኞች ጣቢያ ጋር ለመገናኘት ጥረት እናደርጋለን። መስመሩን ማግኘት አልቻልንም። ብለን ብለን ሲያቅተን እኔና እሳቸው መኪና ይዘን ወደ እንጦጦ ወጣን፤ ፍሪኩዌንሲውን ለማግኘት፤ እውነትም ተገኘ። ከዛ እሳቸው የሚያስፈልጋቸውን መረጃ ሁሉ ጠይቀው ተቀበሉ። ያለውን የእህል ክምችት፣ የተከፋፈለውን፣ የሚያስፈልገውን ሁሉንም መረጃ አገኙ። ወደ እንጦጦ ስንሄድ ክብድ ብሎ የነበረው ፊታቸው ፈገግታ ለበሰ፣ ብርሃን ሆነ። በሠራሁባቸው የስደተኞች ጣቢያዎች ላይ አስቸጋሪ ሁኔታ ሲገጥመኝ ይሄ ስሜት እኔንም ይሰማኝ ነበር።”

ዶ/ር አሸናፊ ስለ ኢንጂነር ጌታቸው አርቆ አስተዋይነት የሚናገሩት ነገር

አላቸው፡- "ስደተኛውን አስቀምጦ ሁሌ መቀለብ ሳይሆን ነገሮች ሲስተካከሉ ስደተኛውን በሰላማዊ መንገድ ወደ መጣበት መመለስ ነው፡፡ እዚህ ላይ ኢንጂነር ጌታቸው ሁሌ የሚሉት አላቸው ‹ስደተኞች በሰፈሩባቸው አካባቢዎች ወፍጮዎች ይተከሉ፣ ትምህርት ቤቶች ይሰሩ፣ ክሊኒኮች ይገንቡ› ይላሉ፡፡ እየው ልጅ አሸናፊ እንግዲህ ስደተኛው ሲመለስ ይቺ አውራጃ ወይ ወረዳ ትሆናለች፣ የአካባቢው ሰው ወፍጮ ይኖረዋል፣ ክሊኒክ ይኖረዋል፡፡ ዛሬ የምናደርገው ነገር ስደተኛውን ማስተናገድ ብቻ ሳይሆን፣ ከተማ መመሥረትም ነው" በማለት አስረድተዋቸዋል፡፡

በገንዘብ አወጣጥ ላይ አቶ ጌታቸው እጅግ ጠንቃቃ መሆናቸውን ያስተዋሉት ዶ/ር አሸናፊ በገንዘብ ዙሪያ የሚሉትም አላቸው፡- "እኔ ከእሳቸው ጋር በቆየሁባቸው ዓመታት አምስት ሳንቲም አለአግባብ ስትወጣ አላየሁም፡፡ ከራሴ ኪስ ይልቅ ኢንጂነር ጌታቸውን አምናለሁ ብዬ መናገር እችላለሁ፡፡ በእሳቸው ዕይታ ገንዘብ አለአግባብ ወጣ ማለት ማባከን፣ ሃገር መሸርሸር ማለት ነው፡፡"

በኢንጂነር ጌታቸው ስብዕና ላይ ዶ/ር አሸናፊ አንድ የተመለከቱት አብይ ነገር አላቸው፡- "በአሉታዊ ሳይሆን በአዎንታዊ መልኩ ከተመለከትነው ኢንጂነር ጌታቸው ራሳቸውን ይወዳሉ ማለት ይቻላል፡፡ የሰው ልጅ ለኃላፊነት የሚበቃው መጀመሪያ ራሱን ወደ ራሱን ሲጠብቅ ነው፡፡ ሰው ራሱን ነፃ ሲያወጣ ነው ለሌላ ሰው የሚቀረቀረው፡፡ በባርነት ላይ ያለ ሰው በባርነት ሥር ላለ ሰው ሙግት ማድረግ አይችልም፡፡ ፍቅር ለራሱ ያጣ ሰው፣ ለሌላ ሰው ፍቅር መስጠት አይችልም" ይላሉ ዶ/ር አሸናፊ፡፡

የኢንጂነር ጌታቸውን የዘወትር ባህሪይና ሁኔታ በመመልከት "ልብሳቸው ሁሌ ጽዱና ያማረ ነው፡፡ አንድ ቀን እንኳን በድንገት ኢንጂነር ጌታቸው ዛሬ ምን ነካቸው? የሚያሰኝ ነገር አይቼባቸው አላውቅም? በማለት ዶ/ር አሸናፊ ለኢንጂነር ጌታቸው ያላቸውን ልባዊ አክብሮት ይገልፃሉ፡፡





# አቶ ገብሩ ሃብተወልድ

## የፋይናንስ ባለሙያ

ስለ ኢንጅነር ጌታቸው የሥራ ታታሪነትና እከሌ ከእከሌ ሳይሉ ሁሉንም የሥራ ባልደረቦቻቸውን በአክብሮት ይመለከቱና ያስተናግዱ እንደነበር በአሁኑ ግዜ የኢንትግሬድ ኩባንያ ባለቤት የሆኑት የፋይናንስ ባለሙያ አቶ ገብሩ ሃብተወልድ መስክረዋል፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው በብሔራዊ ሃብት ልማት ኮርፖሬሽን ውስጥ ዋና ሥራ አስኪያጅ በነበሩበት ወቅት ለኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ የሂሳብ ሹም ሆነው የተቀጠሩት አቶ ገብሩ ሲናገሩ "በድርጅቱ በቆየሁበት ሁለት ዓመት ውስጥ የፋይናንስ መምሪያውን የምመራው እኔ ነበርኩ፡፡ በዛን ወቅት ከአቶ ጌታቸው ጋር በመመካከር ነበር የምንሠራው፡፡ ከእሳቸው ጋር ሥሠራ ምንም ችግር አልነበረብኝም፡፡ አቶ ጌታቸው ሰውን የሚያከብሩ ሰው ናቸው፡፡ የሰውንም ልክ የሚያውቁ ሰው ናቸው" ብለዋል፡፡

ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ በፋይናንስ የተመረቁት አቶ ገብሩ ቀደም ብለው በአውራ ጎዳና መ/ቤት የሂሳብ ክፍል ሹም ሆነው ሰርተዋል፡፡ በብሔራዊ ሃብት ልማት ኮርፖሬሽን ሲቀጠሩ ፈታኞቹ የፋይናንስ ባለሙያዎች የነበሩ ሲሆን ኢንጂነር ጌታቸው በፈተናው ወቅት በተመልካችነት ብቻ ነበር የተወሰኑት፡፡

ድርጅቱ ባለሙያን በማሰባሰብ በዘመናዊ አሠራር የተደራጀው በኢንጂነር ጌታቸው ግዜ መሆኑንና ኢንጂነር ጌታቸው ባለሙያው እስካመነበት ድረስ ምንም ዓይነት ጫና የማይፈጥሩ ኃላፊ

እንደነበሩ አቶ ገብሩ ገልፀዋል።

"አቶ ጌታቸው ሁሉንም የሚያከብሩ፣ ከንጉሳውያንና ከባለስልጣናት ጋር የነበራቸው ግንኙነትና ትልቅነት ሥራ ቦታቸው ላይ ፈጽሞ የማይንፀባረቅ ጨዋ ሰው ናቸው" ብለዋል አቶ ገብሩ። "ከሥራው ዓለም ውጭ ስናነጋግራቸው እንደጓደኛ ነው።"

ኢንጂነር ጌታቸው የባለሙያን ሃሳብ የሚያከብሩ ሰው መሆናቸውን፣ በሥራ ረገድ ከሁሉም ጋር ተግባብተው የሚሠሩ፣ በድምጽ ብልጫ የተወሰነውን ተግባራዊ የሚያደርጉ፣ በድምጽ ብልጫ የተወሰኑ ውሳኔዎችን እማይፈልጉት እንኳን ቢሆን የሚቀበሉ፣ ጣልቃ የማይገቡ ቢሮአቸው የሚገባውን ሰው ሁሉ አክብረው ተነስተው፣ ጨብጠው የሚያስቀምጡ ሰው እንደነበሩ አቶ ገብሩ ገልፀዋል።

አቶ ገብሩ ከፋይናንስ መምሪያው በተጨማሪ ቀደም ብሎ በህንዳዊ ኃላፊነት ይሠራ የነበረውን የፋይናንስ ኮንትሮልን ደርበው ሠርተዋል። አቶ ገብሩ ሥራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቅ በፈለጉበት ግዜ ኢንጂነር ጌታቸው መንገዳቸው ላይ አልቆሙም "የመልቀቂያውን ፈቃድ እሰጥሃለሁ። ግን ሂሳቡን ዘግተህ ነው የምትሄደው" ነበር ያሏቸው።





# አቶ ሚሊዮን ወልደ መስቀል

አቶ ሚሊዮን ወልደመስቀል የኢንጂነር ጌታቸው ማህተመሥላሴ አጎት፣ ወንድም፣ አብሮ አደግ ጓደኛም ናቸው። የአቶ ሚሊዮን አባት ክቡር ፀሃፊ ትዕዛዝ ወልደ መስቀል ታሪኩ የብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ አባት ናቸው። ፀኃፊ ትዕዛዝ ወልደ መስቀል የኢንጂነር ጌታቸው አያት መሆናቸው ነው። እንደዛም ሆኖ ግን አቶ ሚሊዮን ፀኃፊ ትዕዛዝ ወልደ መስቀል ከወለዷቸው ልጆች የመጨረሻውና ትንሹ በመሆናቸው በዕድሜ ከኢንጂነር ጌታቸው ማህተመሥላሴ በጣም የሚያንሱ ናቸው።

የአቶ ሚሊዮን እናት ወ/ሮ ወሰንየለሽ ወ/ገብርኤል አቶ ሚሊዮንን በወለዱበት ግዜ ወዲያውኑ በወሊድ ምክንያት ስለሞቱ አቶ ሚሊዮንን ጡት እያጠቡ ያሳደጉት የኢንጂነር ጌታቸው እናት ወ/ሮ አምሳለወርቅ ክፈተው ናቸው። አቶ ሚሊዮንም ወ/ሮ አምሳለወርቅ እናቴ ናት ነው የሚሉት።

እሳቸውም ስላደጉበት ስለ ኢንጂነር ጌታቸው ቤተሰብ ሲናገሩ ቤቱ የመኖሪያ ቤት ሳይሆን የአንድ አዳሪ ት/ቤት ነበር የሚመስለው። በጣም ሰፊ ነበር። በግዜው እንደ ገበታ የተለመደው ሳጠራ ጠረጴዛ ስለነበር በዛ ስፊ በሆነ የሳጠራ ጠረጴዛ ዙሪያ የብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴና የወ/ሮ አምሳለ ወርቅ ልጆች ብቻ ሳይሆኑ ከባለገር ያመጧቸው፣ በአበል ልጅነትና በዝምድና የሚያሳድጓቸው ልጆች አንድ ላይ ተቀምጠው የቀረበላቸውን ይቋደሳሉ።

በኢንጂነር ጌታቸው ቤት የነበሩ ሠራተኞች በልጆቹና በዋናዎቹ አባ ዎራዎች በከበሬታ የሚታዩ፣ የሚወደዱ እንደነበሩ አቶ ሚሊዮን በአጽንኦት ያስረዳሉ። ሠራተኞቹን በስማቸው የሚጠራቸው አልነበረም።

"አብዬ፣ ጋሼ፣ እንኮዬ ..." በሚል ነበር የሚጠሩት። ሠራተኞቹ

በተሠማሩበት በእንጀራ ቤት፣ በጠላ ቤት፣ በጠጅ ቤት . . . ባለሙያዎች ስለነበሩ በጣም ይከበሩ ነበር። ከዋናዎቹ የቤቱ አስተዳዳሪዎች በተጨማሪ በዛ ቤት ውስጥ ሳደጉ ልጆች ሠራተኞቹ ተቆጣጣሪዎችና ሥነ-ምግባር አስተማሪዎችም ነበሩ። ሥርዓት እያስተማሩ፣ እየተቆጣጠሩ፣ እየተቆጡ አሳድገዋቸዋል። እነ ኢንጂነር ጌታቸውን።

የኢንጂነር ጌታቸው ወንድም፣ እኅት፣ ጓደኛ ዕድሜያቸው ወደ 5 ዓመት ሲሆን ወደ አባታቸው ወደ ፀኃፊ ትዕዛዝ ወ/መስቀል ቤት ተመልሰው፣ አባታቸው ወደ ምንኩስናው ዓለም ሲገቡ እሳቸውም አባታቸውን ተከትለው ኢቲሳ ተክለሃይማኖት ገዳም ቢሄዱም ከኢንጂነር ጌታቸውም ሆነ ከቤተሰቡ ጋር ብዙም መለያየት አልነበረም።

ቅኔያቸውን ተምረው፣ እዛው ቅኔያቸውን ተቀኝተው ግዕዛቸውን ተምረው እድሜያቸው ወደ 13 ዓመት ሲሆን የፈረንጅ ትምህርት በቀጠሉበት ወቅት ወደ ወንድማቸው ወደ ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ ቤት ነበር የተመለሱት። ስለዚህም ከኢንጂነር ጌታቸው ተለይተው አደጉ ለማለት አይቻልም። አቶ ሚሊዮን ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ካናዳ ሄደው ለአራት ዓመት ትምህርት ታቸውን ተከታትለው ባችለር ኦፍ ኮሜርስ ድግሪያቸውን ተቀብለው ወደ ሃገራቸው ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላም ከኢንጂነር ጌታቸው ጋር የላቸው ቀረቤታ በጣም ጠንካራ ሆኖ ቆይቷል።

ኢንጂነር ጌታቸው የራሳቸው ውስጣዊ ጥንካሬ፣ አስተዋይነትና ስብዕና እንዳለ ሆኖ ያደጉበት ሥርዓት በእሳቸው የግል ባህሪ ላይ ያሳደረው ተጽእኖ እጅግ ሥር የሰደደ መሆኑን ይናገራሉ።

ቤቱ ፍቅር የሞላበት መሆኑን ሲያስረዱ ከወ/ሮ አምሳለወርቅ ደግነት እና ቸርነት ነው የሚጀምሩት። ቤቱ ገበታ ተዘርግቶበት የሚውል ቤት እንደነበረ አሁንም ያስታውሱታል። "ኢንጂነር በእንዲህ ዓይነት





የእናት ፍቅርና ቸር ቤት ውስጥ ነው ያደገው። ሁላችንም ጓደኛ ወደ ቤት ይዘን መጥተን፣ አብረን ገበታ ቀርበን ያለውን ተካፍለን በልተን፣ ጓደኞቻችንም እናታችንን እማማ ብለው ስመው ነበር ወደ ትምህርት ቤታችን የምንመለሰው" ይላሉ፣ ኢንጂነር ጌታቸው ከመሠረቱ ለሰው ያላቸውን ጥልቅ ፍቅር ለመግለጽ። ይህ ፀጋና በረከት የሞላበት ቤት ወ/ሮ አምሳለወርቅ በጠና ታመው፣ ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ ታሥረው ንብረታቸው ታግዶ፣ የተወረሰውም ተወርሶ በነበረበት ግዜ እንኳን በሥጋ የማይወለዱ ልጆች ሳይበታተኑ የቆዩበት ቤት ነበር።

የቤቱን ሥርዓት ጠቅለል አድርገው ሲገልጹት፡- "የደግ ሰው ቤት፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለበት፣ ሁል ጊዜ የእግዚአብሔር ሥም የሚጠራበት ቤት፤ ማንም ሌላውን የማያንጓጥጥበት፣ የጥጋብ መልክ የማይታይበት ቤት ነበር" ብለዋል።

ኢንጂነር ጌታቸው ሥራን በጥንቃቄ ከልጅነት ጀምሮ ስለመሥ ራታቸው አቶ ሚሊዮን ሲያስረዱ፡- "ጠንቃቃነቱ አሁን ሳይሆን ከልጅነቱ ጀምሮ የነበረ ነው። አባታችን ማህተመሥላሴ አንድ የሚሠራ ሥራ ሲኖረው ሥራ ውን በቁምነገር ተከታትሎ ከዳር የሚያደርስ ሰው ሲፈልግ፤ እከሌ ጨዋታ ያበዛል፣ እከሌ ይዘናጋል፣ ስለዚህ ጌታቸውን ጥሩ ነው የሚባለው። እሱ ነው የልቤን የሚያደርስ ይላል አባቴ" ብለዋል።

ወደ ኋላ መለስ በማለት የኢንጀነር ጌታቸው ጥንቃቄ በሥራ ላይ ብቻ ሳይሆን በአለባበስ እና በጽዳት አጠባበቅም ረገድ ልዩ ሰው መሆናቸውን ይናገራሉ። "ሁል ጊዜ ልብሶቹ ጽድት ያሉ ናቸው። ፀጉሩ ያምራል፣ ሁለት ይከፍለዋል። ጫማውን እስኪያበራ ድረስ እራሱ ውልውል ያደርጋል። ሁላችንም እንኮራበት ነበር። አባታችንም ሰው ወደ ሌላ ቦታ ለመላክ ሲፈልጉ "እናንተ ቆሻሾች" ‹አትረቡም› ጥሩልኝ ያን ጌታቸውን ይሉ ነበር።"

ኢንጂነር ጌታቸውና አቶ ሚሊዮን ሁለቱም በውጭ ሃገራት ቆይተው ወደ ሃገራቸው ሲመለሱ፣ ኢንጂነር ጌታቸው ቀደም ብለው በመመለስ ሥራ ቢጀምሩም፣ አቶ ሚሊዮን ወደ አገር ቤት ከተመለሱ በኋላም ቅርበታቸው እየጠበቀ እንጂ እየላላ አልመጣም፡፡

አቶ ሚሊዮን ስለ ኢንጂነር ጌታቸው የሥራ ትጋት ሲገልጹ፡"እንቅልፍ የለውም፣ ሥራ ካለ ሥራውን ሳይጨርስ አይተ ኛም፡፡ ጽዱ የሆነ ነገር ይወዳል፡፡ አንድ ነገር ሲጽፍ ማሐከልዋ ላይ የምትሠረዝ ነገር ካለች እንደገና እንዳለ እንደ አዲስ ነው የሚጽፈው፡፡"

እንጂነር ጌታቸው የሰውን ሥራ እንደሚያከብሩ ሁሉ የእሳቸውም ሥራ እንዲከበርላቸው የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ያልመሰላቸውን ነገር አይቀበሉም፡፡ ከበታቾቻቸውም ጋር ቢሆን ሥራ ተበላሽቶ ካገኙ፡- "ለምን እንዲህ ዓይነት የተልከሰከሰ ሥራ ተሠራ በሚል እኔው እራሴ ብሠራውስ በማለት ሥራውን እንደ አዲስ ይሠሩታል፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው ከወንድሞቻቸውም ሆነ ከአባታቸው ይልቅ በዕድሜ ከሚቀራርቧቸው ከክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴ ጋር የበለጠ ቀረቤታ እንደነበራቸው አቶ ሚሊዮን ያስታውሳሉ፡ "ሰይፈ ታላቅ ሰው ነው፡፡ በጣም የተከበረ፣ ጨዋ፣ የሰው ፍቅር ያለው፣ በተሰጠው ኃላፊነት በጣም ጠንካራና ጠንቃቃ ሰው ነበር፡፡ በዛ ላይ ሁለ ገብ ሠራተኛ ሰው ነበር፡፡ ጣሪያ ላይ ወጥቶ ቆርቆሮ የሚመታ፣ ባንቧ ቢሠበር የሚሠራ፣ የእርሻ መኪና የሚነዳ፣ መካኒክ ሆኖ ሞተር አውርዶ የሚሠራ ሰው ነበር፣ ከትምህርትና ከሙያው ሌላ ማለት ነው፡፡ ሁላችንም ከእሱ ትምህርት አግኝተናል፡፡ በተለይ ደግሞ ከጋሽ ጌታቸው ጋር በጣም ይቀ ራረቡ ስለነበረ ከጋሼ ሰይፉ ጋሼ ጌታቸው ብዙ ትምህርት ወስዷል፡፡ ሲቆጣም፣ ትንሽ ቢበሳጭም የሚያበርደውና የሚያቀዘቅዘው ጋሽ ሰይፉ ነበር፡፡"





ኢንጂነር ጌታቸው ብሔራዊ ሃብት ልማት ኮርፖሬሽንን ከአዋቀሩ በኋላ በቦታው ሌሎች ሰዎች በተሾሙበት ወቅት፤ እሳቸው የግል እርሻ ለማቋቋም በወሰኑበት ግዜ ዘመድ አዝማዱ ውሳኔያቸውን እንዲቀይሩ ቢጠይቋቸውም አለመስማማታቸውን ገልፀው ወደ ግል እርሻ መግባታቸውን የሚያሳታውሱት አቶ ሚሊዮን በኢንጂነር ጌታቸው የእርሻ ቦታ ስለተሠሩት ሥራዎች ሲናገሩ፡ "በአካባቢው ቤተክርስቲያን የለም በማለት ቤተ ክርስቲያን አሠርቶ፣ ቀሳውስትም ካህናትም አሰባስቧል፡፡ ጀኔሬተር አስገብቶ መብራት እንዲገባ አድርጓል፡፡ የመስኖ አገልግሎት እንዲኖር አስችሏል፡፡" ብለዋል፡፡

በማህበራዊ ሕይወታቸውም በኩል በጣም ተጫዋችና ተግባቢ መሆናቸውን ነው አቶ ሚሊዮን የሚገልጹት፡- "በሆነ ማህበራዊ ጉዳይ ሰው ሰብሰብ ሲል ሰው የሚኮለኮለው ጌታቸው ባለበት ቦታ ላይ ነው፡፡ ባለቤቱ እያለችም በኋላም ቢሆን ሌቱ ሁሉ እሱን ከቦ ይቀመጣል፡፡ ምን እንደሚያወራቸው አናውቅም፡፡ በቻ ሲስቁ ሲደሰቱ ነው የምናያቸው፡፡ ዳንስ አዋቂ ነው፣ ያውም ለመወዳደር የሚያበቃ፡፡ ግብግ የሄድን እንደሆነ አንድ ያልተስተካከለ ወይ የተዛነፈ ነገር ካለ እንግዳ ነኝ ብሎ አርፎ አይቀመጥም፡፡ ተነስቶ እንዲስተካከል ያደርጋል፡፡ ሥጋ እንኳን ሲቆረጥ አቆራረጡ ካላማ ረው ተነስቶ እንዲህ ነው ብልት የሚቆረጠው ብሎ ያሳያል፡፡"

ኢንጂነር ጌታቸው እናታቸውን ለማስታመም ወደ እንግሊዝ ሃገር በሄዱበት ግዜ የደርግ መንግስት ሊያስራቸው ከሚፈልጋቸው ሰዎች አንዱ ነበር፡፡ ዘመድ እና ጓደኛ ወደ ሃገር እንዳይመለሱ ብዙ ወትውተዋቸዋል፡፡ "ስልክ ተደውሎ ልትታሠር ነው አትምጣ፡፡ በእንግሊዝ ሃገር የነበሩ ኢትዮጵያኖች አትሂድ እዚሁ ሥራ ይዘህ ልጆችህን አሳድግ፣ ዘመዶችህን አግዝ ብለውት ነበር፡፡ የማናችንንም ልመናና ጥያቄ አልሰማም፡፡ የሠራሁት ጥፋት የለም፡፡ ያረጉኝን ያርጉኝ

ብሎ መጣ፡፡ በግዜው እንደ ሞኝ ነበር የተቆጠረው" ብለዋል አቶ ሚሊዮን ኢንጂነር ጌታቸው ስለራሳቸው ያላቸው ንጹህነት ምን ያህል ልበ ሙሉ እንዳደረጋቸው ሲገልፁ፡፡

"ባለፉት መንግስታትም ላይ ሆነ አሁንም ባለው የመንግስት ሥርዓት ላይ የታየውን ስህተት ከመጠቆም ወደ ኋላ የሚል አይደለም፡፡ የበደለውም መንግስት ቢሆን በበጎ ሥራዎች ላይ ከመሳተፍ ወደ ኋላ አይልም፡፡"

የኢንጂነርን የብቸኝነት ኑሮ አስመልክተው ያሉትም አለ፡- "ከእሥር ቤት ሲፈታ ከባድ ሁኔታ ገጠመው፤ ከባለቤቱ ጋር ተፋታ፤ ትዳሩን አክብሮ የሚኖር ሰው ነበር፤ በተፈጠረው አጋጣሚ የሆነው በጣም ያስቆጣል፣ አልህ ያስይዛል፡፡ እሱ ግን ከእንግዲህ አግብቼ፣ ትዳር ይዤ መኖር አልፈልግም፡፡ የብቸኝነት ኑሮ ይሻለኛል፡፡ ትዳርን ሞክሬአለሁ፡ ፡ እግዚአብሔር አልፈቀደውም፣ ትዳሩ አልሠመረም፡፡ እስዋ ናት ጥፋተኛ፣ ወይም እኔ ነኝ ንጹሑ ማለት አልችልም፡፡ እንደገና አግብቼ ሌላ ወንድምና እህት ልጆቼ እንዲኖራቸው አልፈልግም ነበር ያለው፡፡ በቃሉም ፀንቶ ኖረ፡፡"

አቶ ሚሊዮን ወደ ኋላ ተመልሰው ስለ ወንድማቸው ስለ ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ የግል ባህሪይና ችሎታም ያሉት አለ፡፡ ይሄ ችሎታና ባህሪይ በኢንጂነር ጌታቸው ባህሪይም ላይ በጉልህ ይታያል ብለዋል፡ ፡ በተለይ በሥራ ወዳድነትና ሥራዎችን በጽሑፍ መዝግቦ በማቆየት፡፡

በምሳሌ ያነሱት ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ ከሥራ ውጭ ሌላ ዓለም ያለ እንደማይመስላቸው ሁሉ ኢንጂነር ጌታቸውም ጊዜያቸው ሁሉ ለሥራ የተሰጠ ነው ብለዋል፡፡

"ለምሳሌ አባባ በሥራ የመድከም ስሜት ሲታይበት እናታችን ሁላችንንም ከከተማ ይዛን ትወጣለች፡፡ ምግባችን በአገልግል ይያዛል፡፡ በአባባ ኪስ





ያሉ እርሳስና ወረቀት እንዳይኖሩ በታናናሽ እህቶቻችን ተፈትሸው ይወሰዳሉ፡፡ ከዛ በመኪና ወጣ እንላለን፡፡ ወጣ እንዳልን ምሳ እየተበላ ወይ ዘና ስንል በአካባቢው አንድ አዛውንት ወይም የአካባቢው ሰው ከታየ ጥሩት ይሉና ያናግሩታል፡፡ ከዛ የሆነ ነገር ሲመዘግቡ ይፈልጉና ወረቀትና እርሳስ ከኪሳቸው ውስጥ ፈልገው ሲያጡ እኛን አምጡ ይላሉ፡፡ የለንም ስንላቸው ከመሬት ስንጥር ብጤ አንስተው የኮትና የሸሚዝ እጅታቸውን ወደ ላይ ሰብስብ በማድረግ እክንዳቸው ላይ ይጽፋሉ፡፡ ይሄ ዓይነቱ ጉዳይ ተደጋግሞ የተደረገ ነው፡፡ ያቺን ይይዙና እቤት ሲገቡ ያስፋፉታል፡፡

ይህ በጽሑፍ የመመዝገብና ለሥራ ያለ ጠንካራ ትጋት ከብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ ብቻ አይጀምርም፡፡ የእሳቸው አባት ፀኃፊ ትዘዝ ወልደ መስቀል ታሪኩም እንዲህ ያደርጉ ነበር፡፡ "እንኳን ከዘመን ዘመን አሸጋገረህ" ለሚለው ጽሑፍ ሁሉ ኮፒ የሚያስቀር ቤተሰብ ነበር እንኳን በቁምነገር የተመዘገቡ የምርምርና የጥናት ጽሑፎች ይቅርና፡፡

በስተመጨረሻም አቶ ሚሊዮን ያሉት አለ፡- "ጋሽ ጌታቸው አርፎ መቀመጥ አይወድም፡፡ አሁን ጋቢህን ተከናንበህ ወይ ካባህን ደርበህ ቤተ ክርስቲያን እየሄድክ አስቀድሰህ ወደ ቤትህ በመመለስ እረፍ ማለት አለብህ እንለዋል፡፡ አይሰማንም፡፡ የእረፍት መንፈስ የለውም፡፡ ሁሌም በሥራ የተጠጠመደ ሰው ነው፡፡" ብለዋል፡፡

# ምዕራፍ አስራ ሰባት

# ኢንጂነር ጌታቸው ማኅተመሥላሴ በግላቸው የሰጡአቸው አስተያየቶች

# ማሳሰቢያ

## ለተከበራችሁ የግብርና ጠበብቶችና ባለሞያዎች የማክበር ሰላምታዬ ይድረሳችሁ

[ኢንጂነር ጌታቸው ማኅተመሥላሴ በሥራቸው ሕዝብን ከሕዝብ፣ አገርን ከአገር ለይተው የሚያዩበት ዓይን እንደሌላቸው ይና ገራሉ።

ከዚህም የተነሳ ማንኛውም ሰው አንዱ የሠራውን በግዴለሽነት ሲያበላሽ ካዩ ያ ንብረት የሠሪው ብቻ ሳይሆን የአገር ንብረት ስለሆነ ለምን ታበላሻለህ ብለው ይናገራሉ፤ ይጣላሉም። ደህና ሥራ ሲሠራ ሲያዩ በዛው መጠን ይደሰታሉ ያመሰግናሉ። በተለይም ለአገርና ለወገን ጎጂ የሆኑ ሰፋፊ ሥራዎች ውጤት አልባ መሆናቸውን ከተገነዘቡ በነቀፋ መልክ ሳይሆን በአጋርነት ነፃ ሞያዊ አስተያየታቸውን ከማካፈል ተቆጥበው የማያውቁ ሰው ለመሆናቸው በተለያየ ጊዜ በግብርናና በምሕንድስና ሞያቸው በቴሌቪዥንና በሬዲዮ የሰጡዋቸው ማሳሰቢያዎች ምስክሮች ናቸው።

ኢንጂነር ጌታቸው ማኅተመሥላሴ በተለያዩ ጋዜጦች ላይ ልዩ ልዩ አስተያየቶችና የጥናት ጽሑፎች አቅርበዋል። ከብዙ በጥቂቱ በመጽሐፉ መጨረሻ ገጽ ላይ ባለው በሰንጠረዥ በዋናነት





ተጠቅሰዋል። ከእነዚህ ውስጥ አራት አስተያየቶች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተካተዋል።]

ባለፈው ዓመት በአገራችን ላይ ረሐብ በስፋት ተከስቶ አርዳታ በሚለመንበት ጊዜ ለግብርና ባለሞያዎች፣ ለመንግስት፣ ለባለሐ ብቶችና ለኢትዮጵያውያን ግለሰቦች፣ እንዲሁም ለእርዳታ ሰጪ ዎች የነፍስ አድን ጥሪ በሚል መልዕክቴን በጋዜጣ ማስተላለፌ ይታወሳል።

አላማውም፣ ቀደም ብሎ የመንግስት እርሻ የነበሩትንና ለበርካታ አመታት ያለ አገልግሎት የተቀመጡትን መሬቶች ሥራ ላይ ለማዋል ሲሆን፣ እነዚህም ሙሉ ጥናት የማይጠይቁ፣ የመስኖ ቦዮቻቸው (ካናሎች) የተዘጋጁ፣ ለመስኖ የሚአገለግሉ ፓምፖችና ቧምቧዎች የተዘረጋላቸው ስለሆነ የክለሳ ጥናት ከተደረገላቸው በኋላ በአነስተኛ ወጭ ተጠግነው ወዲያውኑ ሥራ ላይ ቢውሉ በርሐብ ለተጎዱና ለታመሙ ሰዎች ጠጋኝ የሆኑ በአጭር ጊዜ የሚደርሱ ሰብሎችን በአንድ ሄክታር ላይ ከ500 ኩንታል በላይ በአመት ሶስት ጊዜ አምርተን እዛው እርሻው ጣቢያ ውስጥ የምግብ ማብሰያ መሳሪያ በመትከል አጣፍጠን በትልልቅ የፕላስቲክ በርሜል በማሸግ ረሐብ ወዳለበት ቦታ እናከፋፍል የሚል ነበር።

ከሰብሎቹም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፣ የተለያዩ የድንች ዓይነቶች፣ የተለያዩ ጎመኖች፣ ቲማቲም፣ ሽንኩርት፣ ቃሪያ፣ የበቆሎ እሸት፣ የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህንና ሌሎችን በአጭር ጊዜ የሚደርሱትን ሰብሎች ባሕረ ሸሽ በሆኑ ለም መሬቶች ላይ ዘመናዊ የመስኖ ዘዴ በመጠቀም ጥሩ ምርት ማግኘት እንደሚቻል በመጠቆም ነበር።

በመሠረቱ ኢትዮጵያ ሰፋፊ ለም የሆነ የዕርሻ መሬት፣ በቂ ለመስኖ

የሚውሉ ወንዞችና ሃይቆች ያላት፣ በዘመናዊ የዕርሻ መሳሪያ ለመጠቀም የተመቻቸ መሬትና ለቁጥር የሚያስቸግር ሥራ የፈታ የሰው ኃይል ያላት፣ በአየር ጠባይዋም ሁሉን ዓይነት ሰብሎች ማብቀል የምትችለው አገራችን ሕዝቧን መመገብ አቅቷት ተርበን እህል በተደጋጋሚ ከሌላ አገር ለማኝ ለመሆናችን የመጀመሪያ ተጠያቂዎቹ የግብርና ጠበብቶችና ባለሞያዎችን ስለሚመለከት ለችግሩ አፋጣኝ መፍትሔ መፈለግ ይኖርባቸዋል የሚል እምነት አለኝ።

ምክንያቱም፡-

1. ምርት እያሽቆለቆለ በመሄዱ ለረሐብ መጋለጣችንን እያወቁ ምርት ጨምሯል እያሉ የበላዮቻቸውንና ሕዝባቸውን በማሳሳታቸው፣
2. ምርትን የሚጨምሩና ድርቅንና በሽታን የሚቋቋሙ ዘሮችን በስፋት ለገበሬዎች አከፋፍለናል በማለት የተስፋ እንጀራ ሕዝባቸው እንዲጠብቅ በማድረጋቸው፣
3. በግብርና ላይ የነበሩት የግል ገበሬዎች ከዕርሻው ላይ ሲፈናቀሉ እነሱን የሚተኩና የተሻለ ምርት የሚያስገኙ ተቋሞች በስፋት ባለማደራጀታቸው፣
4. ለዘመናዊ የዕርሻ መሳሪያዎች አጠቃቀም እጅግ በጣም ምቹ የሆኑ፣ የማዳበሪያ ፍላጎታቸው በጣም ጥቂት የሆነ፣ እጥፍ ድርብ የሆነ ሰብል ሊሰጡ የሚችሉትን፣ የላይ አፈራቸው ጥልቅ የሆነ የእርሻ መሬቶችን ለከተማ ማስፋፊያና ለኢንዱስትሪ መቋቋሚያ ሲወስዱ የግብርና ባለሞያዎቹ ዝም ብለው አሳልፈው በመስጠታቸው፣





5. እንዲሁም ለም ባልሆኑ መሬቶች ላይ ከፍ ያለ መጠን ማዳበሪያ ቢጨመርበት እንኳን አጥጋቢ ሰብል ከማይሰጡ መሬቶች ላይ በሚገኝ ሰብል ርሃብን ለማስወገድ በማሰባቸው፣
6. ጋራና ሸንተረሩ ለደን መተኪያ መዋል ሲችሉ ለርሻና ለፍራፍሬ ዛፎች መትከያ የሚውለውን ደልዳላ መሬት ለዛፍ መትከያ ሲውል ባለመቃወም አብረው በመሳተፋቸው፣
7. በተለያየ ጊዜ ከአንድ ዓመት በላይ በችግኝ ማፍያ ጣቢያ ላይ ያልቆዩ ድርቅንና ሌሎችንም ችግሮች መቋቋም የማይችሉ የዛፍ ችግኞችን በያሉበት ተተክለው በእንክብካቤ እጦት አብዛኛው መድረቁን እያዩ ስህተቱን ለማረም አለመሞከራቸው ሲሆን ሌላው ቢቀር ችግኞቹ በችግኝ ማፍያ ላይ እስኪጠነክሩ ቢቆዩ ኖሮ ችግሩን ለመቋቋም አቅም ያገኙ ነበር፣ ይህም አልታሰበበትም።

ለግብርናው ክፍል ያለኝን አጭር ማሳሰቢያ በዚህ ላይ እያቆምኩ በሌላው እጅግ አሳሳቢ በሆነው ልማት ላይ አስተያየቴን እቀጥላለሁ።

ይኸውም፣ የእንስሳት ሃብታችንን በተመለከተ ነው።

ኢትዮጵያ አገራችን በእንስሳ ሀብቷ ከአፍሪካ በአንደኛ ደረጃ ላይ ያለችስት ሆን ለአገር ውስጥ የሥጋ ፍላጎትም በበቂ ሁኔታ ስታቀርብ ቆይታለች። ይህንንም ሃብታችንን እየተንከባከቡ ያቆዩት ግለሰብ የከብት አርቢዎች ሲሆኑ ከባሕላዊ የአረባብ ዘዴ ብዙም አላለፉም።

በአሁኑ ጊዜ ሃብታም አገሮች የሥጋ እጥረት ስላጋጠማቸው የአገራችን ገበሬዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታና ለውጭ አገር በእርድና በቁም ከብት መልክ ከብት ለሚሸጡ ነጋዴዎች እያቀረቡ ነው።

በተጨማሪም በኮንትሮባንድ የሚሸጠው የቁም ከብት ከሕጋዊው ሽያጭ አይተናነስም።

ባጠቃላይ በየቀኑ ለእርድና ለሽያጭ የሚቀርበው የቀንድ ከብት፣ በግና ፍየል፣ ሌሎችም እንስሳቶች ብዛት በየቀኑ ተወልደው፣ አድገው፣ ከተፈጥሮ የሞት አደጋ ተርፈው ለእርድ እድሜ የሚደርሱትና የሚታረዱት እንስሳቶች በጣም ያንሳሉ። ምክንያቱም ለእርባታ ጣቢያዎች ትኩረት ባለመሰጠቱ ነው።

የእርድ ከብት እጥረት ለመኖሩ ሌላው ጠቋሚ ምልክት በጥቂት ጊዜ ውስጥ የሥጋ ዋጋ በየቀኑ ከሚጠበቀው በላይ እየጨመረ የሄደ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ ከቀጠለ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በውድ ዋጋ ሥጋ የመግዛት አቅም ስለሌለው የበይ ተመልካች እንዳይሆን ያሰጋል።

ስለዚህ የግብርና ባለሞያዎች ለም መሬታቸውን በሌሎች አስወስደው ሕዝባቸውን የዳቦ ያለህ እንዳሰኙት እናንተም የእንስሳት እርባታ ጠበብ ቶች ከእርባታው የውጤት ያለህ የምትሉበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም።

ስለዚህ፡-

1. ለእርድና ለሽያጭ የሚቀርቡት የእንስሳት ብዛት ተወልደውና አድገው ለእርድ ብቁ እድሜ ካላቸው እንስሳት ብዛት ጋር ተ መጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ፣
2. በእርድና በቁም የሚሸጠውን የእንስሳት ብዛት የሚተኩ በርካ ታ የእርባታ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ ብርቱ ጥረት ማድረግ፣
3. ዘመናዊ የሆኑትን የእርባታ ዘዴዎች በስፋት በመጠቀም የወ





ተትና የሥጋ ምርትን ማሳደግ ኃላፊነቱ የባለሞያዎቹ ስለሆነ በማዳቀሉ ሥራ ላይ ቢሰማሩ፣

4. በመጧጧፍ ላይ ያለው ሽያጭ ያለንን የእንስሳት ሃብታችንን አሟጦ እንደ እህል እጥረቱ የሥጋ እጥረት ተፈጥሮ ሥጋ ለ ማኝ እንዳንሆን አቅርቦቱና ሽያጩ ተመጣጣኝ የሚሆንበትን ሥርዓት በማጥናት በመንግስት ደረጃ ማስወሰን፣
5. በሥጋና በእንስሳት ንግድ ላይ የተሰማሩት ነጋዴዎች የግል ጥቅማቸውን ብቻ ሳይመለከቱ ወገናቸው ለዘመናት የለመደው ን ሥጋ እንዳያጣ፣ አገራችንም የእንስሳት ሃብት ደሃ እንዳ ትሆን፣ ንግዳቸውም እንዳይቋረጥ ሁላችንም በሕብረት እንድ ንሠራ ኢትዮጵያዊነታችን ያስገድደናል እያልኩ መልዕክቴን በ ትህትና አስተላልፋለሁ።

ጌታቸው ማኀተመሥላሴ<br>
አጠቃላይ የእርሻ ባለሞያ<br>
ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም.

# ስለአዲስ አበባ የከተማ ልማት፣ ፕላን ኢንግዚኪሽንና ሕዝባዊ የውይይት መድረክ አስተባባሪ የቀረቡ አስተያየቶች

## ለክለሳ ጥናቱ የሚረዱ ሃሳቦች

<u>ተራ ቁ. 1</u>

የአዲስ አበባ ከተማን ሕዝብ ለማስተናገድ ከተጠቀሱት አራት አማራጮች ውስጥ የትኛው ይሻላል የሚል ነው።

- የአዲስ አበባ ነዋሪ ቁጥር በቀድሞው ማስተር ፕላን እቅድ መሠረት 900,000 ሺህ ነበር።

  በመሠረቱ የአንድን ከተማ ሕዝብ ብዛት ለመወሰን ከአየር ንብረቱ በተጨማሪ እንደ ውሃ፣ ምግብ፣ ማገዶ ወዘተ የመሳሰሉት ዋና ዋና አቅርቦቶች በብቃትና በመጠነኛ ዋጋ ሊገኙ መቻላቸው ሲረጋገጥ ነው።

  ነገር ግን እንደ እቅዱ መሆኑ ቀርቶ በሥራ ፍለጋ ምክንያት ከገጠር ፈልሶ የመጣው ሕዝብ ከተማዋን ስላጥለቀለቃት የነዋሪው ብዛት ወደ 1,500,000 እንደሚደርስ በመገመቱ ክልሉም በዛው መጠን እንዲሰፋ ተደረገ። መገልገያዎችንም ለማሟላት ከርቀት ማምጣት ስላስፈለገ የኑሮ ወጪ እያደረገ ሄደ።

  አሁን ይባስ ብሎ ሕዝቡ ከ3 ሚሊዮን ወደ 6 ሚሊዮን እንደሚደረስ ተጠቅሷል። ይህ ከገጠር ወደ ተለያዩ ከተሞች በተመሳሳይ በብዛት የመፍለሱ ጉዳይ ገጠሩንም ከተማውንም እጅግ የሚጎዳ በመሆኑ ሁኔታውን የተገነዘብነው ባለሞያዎች ጥቅምና ጉዳቱን በሰፊው ማስረዳት ኃላፊነት አለብን።



በላንድስኬፕ አርክቴክት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ

ለምሳሌ ገጠሬው ሲሰደድ የገጠር ልማት ይወድማል፣ ከገጠር ምግብና የፋብሪካ ጥሬ እቃ ሲቋረጥ ፋብሪካዎች ሥራ ያቋርጣሉ፣ ሕዝቡም ሥራ ፈቶና ረሐብተኛ ይሆናል። በዚህን ጊዜ ችግሩ የጥቂቶች መሆኑ ቀርቶ የአገር ችግር ሆነ ማለት ነው።

ስለዚህ

- ኢንዱስትሪዎች በገጠር ከተሞች አካባቢ እንዲቋቋሙ መገፋፋት
- የግብርና ዘዴዎችንና የገበሬውን ኑሮ ማሻሻል ሲሆን፣ በገጠር ከተሞች የቁጠባ ቤቶችን በመስራት ችግሮችን ማቃለል፣ የጥሩ መጠጥ ውሃ፣ የመብራት፣ የትምህርት ወዘተ ተቋማቶችን በማሟላት ፍልሰትን በያለበት እንዲቆም ከማድረጉም በላይ አሁን በየከተማው ያለውን ሥራ የማጣት ፈተና ለመወጣት ባለሙያዎች ፊታቸውን ወደ ገጠሩ እንዲመልሱ ያደርጋል።

<u>ተራ. ቁ. 2</u>

(ሀ) እንደተጠቀሰው ከሁሉም የልማት እቅድ ቅድሚያ የሚሰጠው በማስተር ፕላኑ መሠረት መሐል ከተማ ባለው ባዶ ቦታ፣ ባረጁና ለከተማው ውበት እንቅፋት የሆኑትን ቤቶች አፍርሶ ዘመናዊ ሕንፃዎችን ወዲያውኑ መተካት ከግዴታም በላይ ግዴታ ነው፡፡ ነገር ግን ታሪካዊ የሆኑ ቤቶችንና የታሪክ ቅርሶችን በአግባቡ ጠብቆ ቢቻል ለጉብኝት ማብቃት ሌላው ግዴታ ነው።

(ለ) ቀበሌ በአስተዳደር ላይ ብቻ ቢያተኩር ይመረጣል። ይህም ስልጣን ሊሰጠው የሚገባው አስተዳደሩ በተማረና በሰለጠነ ሰው ከተዋቀረ ነው። ደህና አስተዳደር ከሌለ ለልማት እንቅፋት ስለሚሆን

ባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ ሥራ ላይ ቢያተኩር ይሻላል።

(ሐ) በ(ለ) ላይ እንደተጠቀሰው ሳተላይት ከተሞችን ባስቸኳይ መፍጠሩ አንዱ አማራጭ ነው። ሌላው ቢቀር ያልሰለጠነውን ባላገር በቅድሚያ ተቀብሎ በማስተናገድ የከተማን ኑሮና ሥራን ያለማም ደዋል። እንዲሁም በከተማው ዙሪያ የግብርናን ሥራ ለሚያራምዱ ድርጅቶች ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ተራ.ቁ.3

- በሕገ ወጥ መንገድ ትልቅም ሆነ ትንሽ ቤት ከተሠራ አጥር ካጠረ በዞኑ ቴክኒክ ክፍል ሲረጋገጥ ዞኑ የማስፈረስ ስልጣን ቢሰጠው ስሕተቶችን ያቃልላል። የመጠቆሙንና የማፍረሱን ሥራ በዞኑ እያስወሰነ ቀበሌው ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል።
- ነገር ግን ሕገወጥ ሥራ ለምን ተፈፀመ የሚለው ጥያቄ መልስ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ደሐም ሆነ ሐብታም የኢትዮጵያዊነት መብቱ ከተጠበቀለትና ለችግሩም መፍትሔ ከተሰጠው ሕግን ተላልፎ ላይሠራ ይችላል።
- በ(ሀ) እና (ለ) እንደምንመለከተው መጠለያ በማጣት ከባለጠጋ ውሻ ያነሰ ኑሮ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ምንም ነገር ቢሠራ ተወቃሽ ሊሆን አይችልም የሚል እምነት አለኝ።

<u>ተራ.ቁ. 4</u>

በ(ሀ) እና (ለ) የተጠቀሱት ጎን ለጎን ቢሄዱ ችግሩን በፍጥነት ያቃልላሉ። በተጨማሪም የባንክ እገዛ ቢመቻችላቸው እጅግ ጠቃሚ ነው።

<u>ተራ.ቁ. 5</u>

በ(ሀ) ላይ እንደተጠቀሰው በመሐል ከተማ የሚገኙ የማስተር





ፕላኑን ደረጃ የማይጠብቁ ቤቶችን አፍርሶ ወዲያውኑ በዘመናዊ ሕንፃዎች መተካት አጠያያቂ ሊሆን አይችልም።

- በእኔ አስተያየት የሚፈርሰው ቤትም ሆነ ቦታ ባለቤት በጊዜው የገበያ ዋጋ ትክክለኛ ግምቱን እንዲያገኝ ማድረግ፣ ያስፈልጋል።
- ባለቤቱ በሚቀበለው ግምት በፕሮጀክቱ ተሳታፊ ለመሆን ፈቃደኛ ከሆነ እድል እንዲሰጠው፣
- ግምቱን ተቀብሎ ከለቀቀ በሚከፈለው ገንዘብ የፈለገውን ማድረግ መብቱ ስለሆነ ከመንግስትም ሆነ ከሌላ የሚጠይቀው ምንም አይነት ግዴታ እንደሌለው በቅድሚያ እንዲገነዘብ ማድረግ ተገቢ ነው።
- ለሚለቀው ቦታና ቤት በበኩሉ የተሻለ ገገር ካገኘ መሸጥ መብቱ መሆኑ ቢረጋገጥና ገዥው ግን ማስተር ፕላኑ የሚያዘውን ሁሉ የማሟላት ግዴታ እንዳለበት አውቆ መግዛት አለበት።
- አዳዲስ የመኖሪያ ቤቶችን በማስተር ፕላኑ መሠረት ለግላቸው መኖሪያ ለሚሠሩ ሰዎች ቦታ ሸንሽኖ በመጠነኛ ዋጋ በረጅም ጊዜ ክፍያ መስጠቱ ጠቃሚ ነው። ኢንቬስተሮችም ቢሆኑ ቤቶችን ሠርተው ለማከራየት ሳይሆን ሠርተው ለመሸጥ ከሆነ የቦታው ሽያጭ በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲፈፀም ሆኖ ትርፋቸው በኮንስትራክሽንና ሌላም በስምምነታቸው መሠረት በሚያወጡት ወጭ ብቻ መሆን ይኖርበታል።
- ቤት አሠሪዎች ከተቋራጭ ኩባንያ ቤታቸውን በሚረከቡበት ጊዜ የባንክ ብድር ለአሠሪዎች መመቻቸት ይኖርበታል።
- የመንግስታና የዕርዳታ ሰጭዎች ተሳትፎ መኖር ያለበት በቁ

ጠባ ቤት የጊዜአዊ የቤት ችግሮችን ለማቃለል በጠነከረ ሁኔታ መሳተፍ አለበት። ይኸውም በዝቅተኛ ዋጋ ዋናውን ልማት በማያደናቅፉ ቦታዎች ላይ ጊዜአዊ ቤቶችን ሠርቶ ማከራየት ላይ ነው።

እነዚህ ቤቶች ምንም መጠለያ የሌላቸው፣ ለጊዜው አነስተኛ ገቢ ላላቸውና ከተለያዩ ቦታዎች ጭምር መጥተው የተሻለ ቤት እስከሚሰሩ ለማረፊያ የሚጠቀሙበት ከጨረቃ ቤቶች ተቀራራቢ የሆነ፣ የልማት ፕሮጀክት ቢደርስባቸውና ቢፈርሱ ኪሳራ የማያመጡ ዓይነት ቤቶች ላይ ማተኮሩ ውጤቱ የጎላ ነው። በ2ኛው ዓለም ጦርነት ጊዜ ከተሞቻቸው የወደሙባቸው አገሮች በተለይም ጀርመን ጋርደን በሚል ሠፈራ አዘጋጅተው በረንዳዋንና አትክልቷን ለቀን ውሎ፣ ቤቷን ለቀሪው ጊዜ እየተጠቀሙ ከቆዩ በኋላ ቤት ሠርተው ሲለቁ ሌላው ችግረኛ ይተካል።

<u>ተራ.ቁ.6</u>

የሊዝ ስርዓትን በመሠረቱ አጥብቄ እቃወማለሁ። ምክንያቱም ገንዘብ ያለው ሁሉ እየተጫረተ ከተማዋን በሙሉ ሊገዛት ይችላል። እየተገዛም ነው።

መንግስት የግለሰቦችን አንጡራ ሃብት ቀምቶ ለሌላ ሰው መስጠትም ሆነ መሸጥ ፈጽሞ ሕጋዊ አይደለም። ከአንድ ሕዝብን በእኩልነትና በፍትህ ከሚያስተዳድር መንግስት የሚጠበቅ ውሳኔ ሊሆን አይችልም። ተገቢ መሆን የሚችለው ግለሰቦቹ በሕገወጥ የያዙት መሬትና ቤት ሌላም ንብረቶች ከሆኑ መውረስ ብቻ ሳይሆን ሕገ መንግስቱ በሚያዘው መሠረት መቀጣትም ይኖርባቸዋል። ደርግ በጥላቻ ላይ በተመሠረተ ያለ ፍርድ የወረሰውን ቤት ቦታና ሌላም ማንኛውንም





ዓይነት ንብረት ለባለመብቱ መመለስ ወይም በጊዜው የገበያ ዋጋ ግምቱን መክፈል ፍትህ ባገሪቱ ላይ መኖሩን ያረጋግጣል።

በተራ.ቁ.6 የሊዝ ስርዓት መባሉ ቀርቶ የመንግስት ሕጋዊ መሬቶችን ለመሸጥም ሆነ ለማከራየት በሚል ቢተካና በሀ፣ ለ፣ ሐ በተጠቀሱት ላይ መንግስት የሕዝቡን አቅም መሠረት በማድረግ በሁሉም ላይ የዋጋ አስተያየት እያደረገ ቢወስን መብቱ ነው እላለሁ።

<u>ተራ.ቁ.7</u>

የከተማችንን እድገት ለማፋጠን በ(ለ) እንደተጠቀሰው ጥሩ ውጤት ከማስገኘቱም በላይ አፋጣኝ ውሳኔ ለማግኘት ይረዳል።

<u>ተራ.ቁ.8</u>

የመሐል ከተማን ለማሻሻል ባለሙያዎች የማስተር ፕላንን ሕጎች በትክክል ተከትለው ቅድመ ጥናት ካዘጋጁ በኋላ በተቻለ መጠን የሃገር ውስጥና የውጭ ባለሙያዎች እንዲሁም የበሰለ አስተያየት የሚሰጡ ግለሰቦችና ኢንቨስተሮች በጥናቱ ላይ ከተቹበት በኋላ ጠቃሚ የሆኑ አስተያየቶች ታክሉበት ጥናቱ እንዲጸድቅ ማድረግ።

በሂደት ላይ ከሚአጋጥሙ ጉልህ ለውጦች በቀር የጸደቀው ጥናት በትዕ ዛዝ እንዲለወጥ የሚያደርጉ ጣልቃ ገቦች ጨርሶ አስፈላጊ አይደሉም። የፕላን ክፍል ከየትኛውም ክፍል ለማንኛውም ጉዳይ ለሚቀርብ ጥያቄ በጥናቱ መሠረት አፋጣኝ መልስ ከሰጠ የነዋሪው ሕዝብ ፍላጎት ተሟላ ማለት ነው።

<u>ተራ.ቁ.9</u>

በአዲስ አበባ ክልል ውስጥ ያሉ ባለሥልጣኖች፣ ባለሞያዎችና ነዋሪዎች ከሌላው ክልል ሁሉ የተሻለ ምሁር፣ ባለሙያ ያለው ስለሆነ የማንም ጣልቃ ገብነት ሊኖር አይገባም። ይልቁንም ሌሎች

ክልሎች ከክልል 14 ብዙ እውቀት ሊገበዩ ስለሚችሉ የእርዳታ ጥያቄው መምጣት ያለበት ከክልሎች ነው እላለሁ። ክልል 14 በፖሊሲ ቅንጅት ማድረግ ከሚገባቸው መ/ቤቶችና ነዋሪው ሕዝብ ጋር እየተገናኘ በጥናቱ ጊዜ ፍላጎታቸው በተገቢው ሁኔታ ስለመሟላቱ ለመገንዘብ የሐሳብ መለዋወጥ ማድረግ ግዴታው ነው።

ተራ.ቁ.10

የአዲስ አበባ ከተማ መሠረተ ልማት አውታሮችን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ ከነዋሪው ሕዝብ በቂ ታክስ ማግኘት የማይካድ ነው። አስከፊው ጉዳይ ለሚከፍሉት ታክስ ተመጣጣኝ ሰርቪስ አለማግኘቱ ላይ ነው።

ሀ) ከሁሉ አስቀድሞ ለነዋሪው ሕዝብ ክልሉ ምን ዓይነት አገልግሎቶችን ለመስጠት አቅዷል የሚለው የተሟላና በባለሞያ የተጠና ጥናት መዘጋጀት አለበት።

ለ) በጥናቱ መሠረት አገልግሎት ለመስጠት ምን ያህል ወጪ ይጠይቃል የሚለው አሁንም በባለሙያዎች ይተመናል።

ሐ) በጥናቱ መሠረት የተተመነውን ገንዘብ ከነመጠባበቂያው ነዋሪው ሕዝብ በታክስ መልክ መክፈል ግዴታው ነው።
ከዚህ ውጭ በልዩ ተሳትፎ የሚጠየቅ ወጪ ግን መፈፀም የሚችለው በሕዝቡ በጎ ፈቃድ መሆን ይኖርበታል።

ተራ.ቁ. 11

የቀለበት መንገድ ለከተማይቱ የኤኮኖሚና የልማት እመርታ ይፈጥራል በሚለው አጠቃላይ አነጋገር እስማማለሁ። ይሁንና የቀለበት መንገዱ የመንገድ ትራፊክን በከፍተኛ ደረጃ ከማቃለሉም በላይ ጊዜን ይቆጥባል፣ የትራፊክ መጨናነቅን ይቀንሳል፤ በመሠረቱ የአዲስ አበባ ከተማ አቀማመጥ ወጣ ገብና ተዳፋት ያለው በመሆኑ





ሌሎቹን አይነቶች የከተማ አቀያየስ ዘዴ ለመጠቀም አመች ባለመሆኑ የቀለበት መንገዶችን ዘዴ መጠቀም አማራጭ ሁኖ ተገኘ። ስለዚህም የአዲስ አበባ ከተማ 3 የቀለበት መንገዶች ነበሩት። አሁን በመሠራት ላይ ያለውም ሶስተኛውና በከተማው ዳርቻ የተቀየሰው ነው።

ይህ የቀለበት መንገድ የራሱ ጥቅም ሰጭነት ያለው ሁኖ ሳለ የማስተር ፕላኑን ተግባር ለምን ከቀለበት መንገዱ ጋር ለማያያዝ ተፈለገ።

ስለዚህ የመሬት አጠቃቀሙንም ሆነ የልማቱን ሁኔታ መደልደልና መወሰን ያለበት በማስተር ፕላኑ መሠረት ቢሆን ትክክለኛ ነው የሚል አስተያየት አለኝ።

ተራ.ቁ.12

የመርካቶን አካባቢ ጭንቅንቅ ለማስወገድ የታቀደው እቅድ ትክክለኛና አፋጣኝ እርምጃን የሚጠይቅ ውሳኔ ነው።

ሀ) ስለገበያዎች የተጠቀሱት ቦታዎች አሁንም ቢሆን መወሰን ያለባቸው ማስተር ፕላኑ በሚፈቅደው ቦታዎች ላይ መሆን ይኖርባቸዋል። የተሻለውም አማራጭ በዋና ዋና የመግቢያ በሮች ላይ በሆን ጥሩ ነው።

ተራ.ቁ.13

ለወደፊት የከተማችን የመኖሪያ ቤቶች አሠራር የቀረቡት ሁለቱም ሃሳቦች መኖር ይገባቸዋል።

ሆኖም በማስተር ፕላኑ መሠረት የሕዝቦች በአንድነት መሰብሰብ ግዴታ ነው። ምክንያቱም ከቦታ ቁጠባ፣ ከትራንስፖርት፣ በአጠቃላይ የአገልግሎት ሰጪ አውታሮችን ወጪ ለመቆጠብ፣ ለከተማ ድምቀት፣ የሥራ እንቅስቃሴዎችን ለማቀራረብና የመሳሰሉ ብዙ ጥቅሞች ለማግኘት ይረዳል።

የግል ግቢን በተመለከተ ፕላኑ ላይ በተከለሉ ቦታዎች ላይ እንደ ሌላው አገር ሁሉ እኛም አገር መኖር አለበት። በበኩሌም በግል ቤቶች አሠራር ላይ በጥብቅ የምቃወመው ነገር አለ። ይኸውም እንደ አሥር ቤት የሚገነቡ ለአካባቢው የከተማ ውበት አስከፊ የሆኑ ግምቦችና አጥሮች ናቸው። እነዚህ ሁኔታዎች የቤት ሥራ ፈቃድ በሚሰጡበት ጊዜ መስተካከል የሚችሉ ስለሆነ እንደትልቅ ችግር በበኩሌ አልቆ ጥረውም። ቢቻል አጥሩ ብቻ ሳይሆን የሚሰሩ ቤቶች አንዱ የሌላውን ቤት ውበትና አቀማመጥ የሚያዳብር መሆን ይኖርበታል። ይህም በፈቃዱ ጊዜ ሊታረም ይገባል እላለሁ።

ተራ.ቁ.14

በአዲስ አበባ የመካነ መቃብር ችግር እጅግ አሳሳቢ ለመሆኑ ትኩረት እንደተሰጠው ሁሉ በአፋጣኝ የተሻለ ዘዴ ፈጥሮ ተግባር ላይ ማዋል አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው።

ከቀረቡት ሃሳቦች ውስጥ፣

- የቦታ አባካኝነት በዋንኛነት የሚጠቀስ ሲሆን ትላልቅ ሐውልቶችም ለችግር አስተዋጽኦ አላቸው።
- በመሠረቱ የመቃብር ቦታ በዘፈቀደ ሥራ ላይ መዋል የለበትም ባለሙያው በትንሽ ቦታ ላይ ብዙ አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል ሁኔታ በቦታው ፕላን ላይ በትክክል ማስፈር አለበት።

የተለያየም የአቀባበር ሁኔታ አለ። ለምሳሌ እራስና እራስ፣ እግርና እራስ፣ በአትክልት በተከበበ ሁኔታ ለቤተሰብ ሐውልት ያለው፣ ሃውልት የሌለው፣ የወታደሮች የመሳሰሉት ናቸው። የእያንዳንዱ አይነት የራሱ የስፋትና የቁመት መጠን አለው። የቀብሩ ቦታ የይዞታ ዘመን ከቦታ ቦታ በመጠኑ ቢለያይም በአብዛኛው ለትልቅ ሰው ከ20-25 ዓመት፣





እስከ 10 ዓመት እድሜ ላለው 20 ዓመት፣ የሶስት ዓመት እድሜ ላለው እስከ 15 ዓመት ይፈቀዳል። የቦታ ጥበት ላለበት ከተማ የአፈር እርጥበት እስከሌለው ድረስ ጊዜውን ማሳጠር ይቻላል።

የፉካ አሠራር ከመሬት በታች ያለው ሳይቆጠር ከመሬት በላይ በአትክልት በተከበበ ውስጥ እስከ 1.25 ሜትር፣ ከግንብ ጋር ተለጣፊ ሲሆን እስከ 1.50 ሜትር የተለመደ አሠራር ነው።

ይህን ጉዳይ ዘርዘር ባለ ሁኔታ ላቀርብ የፈለግሁበት ዋናው ምክንያት በአንዳንድ የቤተክርስቲያኖች መቃብር ቦታዎች ላይ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከመሬት በላይ ፎቆች በመሥራትና ፉካ በማውጣት የቀብር ቦታነት ምልክት በሌለውና ባልተዛመደ ሁኔታ ሲገነባ በማየቴ ነው፡ ፡ በመሠረቱ ቀብሮች መከናወን ያለባቸው በተቻለ መጠን ከመሬት ወለል በታች መሆን አለበት። ሌላው ቢቀር ባልተጋለጠ መልክ ለምሳሌ በቅድስ ጊዮርጊስና በቅድስት ስላሴ ካቴድራሎች የተሠሩትን ተመልክቶ ቅዱስ ሚካኤል ከተሠራው ሕገ ወጥ ሕንፃዎች አሠራር ጋር አመዛዝኖ የወደፊቱን ጥናት መወሰን ይቻላል። የቀብር ቦታዎች ሥርአቱን ተከትለው በቤተክርስቲያን ሥር፣ በግል ድርጅትና፣ በእድር ማዘጋጀት ይቻላል። የትም አገር እንዳለው ሁሉ ፍታቱን፣ የቀብር ሥርአቱን፣ መኪናውን፣ አበባውን አዘጋጅቶ የሚች ቤተሰብ ሳይቸገር ሥርአቱን ይፈጽማል። የመቃብር ቦታን ስፋት የሚወስነው የከተማው ሕዝብ ብዛት ነው። ዝርዝሩ ትንሽ ሰፋ ስላለ ትቸዋለሁ።

ተራ.ቁ. 15

ከአዲስ አበባ ነዋሪ 70% ደምበኛ እግረኛ ሌላው 20% ደግሞ ከቢሮና ከሱቅ የሚወጣ ባለመኪና ሲጨመር 90% ነው ማለት ይቻላል።

ይህ ብዛት ያለው እግረኛ፣ ቁጭ ብለው የሚነግዱ ተዘዋዋሪ ባለሱቆች ናቸው ወይንስ ማዘጋጃ ቤት እራሱ ነው በመንገዱ መጣበብ ተጠያቂ

መሆን ያለበት፡፡ በመሠረቱ ለሕጎች መጣስ መንስኤው ምንድነው ብለን ብንጠይቅ፣

- በሕዝቡ መጠን በቂ ስፋት ያለው የእግር መንገድ አለ ወይ
- ለተዘዋዋሪና በመንገድ ላይ አንጥፈው ለሚነግዱ ሰዎች ሕጋዊ የተከለለ የገበያ ቦታ አለ ወይ የሚለው ጥያቄ ሕጋዊ ነው ብዬ እምናለሁ፡፡

<u>የበኩሌን አስተያየት ብሰጥ፣</u>

- በየትኛውም አቅጣጫ ብንሄድ አሁንም ሆነ በፊት ለእግረኛው የሚመጥን የእግር መንገድ የለም፡፡ በተለይም በሱቆችና በትምህርት ቤት አካባቢ፣ ከከፍተኛ ፎቆች ለሚወጡ ብዛት ያላቸው የቢሮ ሠራተኞች አመቺ የእግር መንገድ የለም፡፡ እንደ መኪና መንገዱ በለሠለሠና አመቺ በሆነ ሁኔታ ተጠግኖ መዘጋጀት አለበት፡፡
- በተለይ አሁን ለፍሳሽ ተብሎ የተሠራው ቦይ የእግር መንገዶችን ገምሶ ከወሰደ በኋላ ለእግረኛ ተተኪ መንገድ ባለመኖሩ በመኪናው መንገድ መጠቀም ተገዶ የለምን?
- እግረኛ ሲባል ሕፃናትን፣ ሽማግሌዎችን፣ አይነ-ሥውሮችን፣ አካል-ጉዳተኞችን የሚያካትት መሆኑ እየታወቀ አካል ጉዳተኞች ለአደጋና ለችግር አልተጋለጡምን?
- ለእያንዳንዱ ቦታ በዩ አስፋልቱ ጠርዝ ለመድረስ ምንም ሳይቀረው መኪና ከአደጋ ሲሸሽ ቦዩ ውስጥ የሚገባው ሰው ጉዳቱ ቀላል ነውን?
- ሕዝቡ ባልተጠገነና ጨርሶም ተገቢ የእግር መንገድ በሌለበት ቦታ መኪና መንገድ ውስጥ በመግባት ተገዶ አደጋ ቢደርስ ማነው ተጠያቂ?





ስለዚህ እግረኛ በእግር መንገድ ላይ እንዲጓዝ፣ ሲአቋርጥም በነጭ መስመር በተሠመረው ቦታ እንዲአቋርጥ፣ እነዚህንና ሌላም ያልጠቀስኳቸው የእግረኛ መብቶች በማዘጋጃ ቤቱ ከተሟሉ በኋላ እስከ መቅጣት ድረስ የሚያደርስ አስገዳጅ መመሪያም ሆነ አዋጅ ማውጣት ተገቢ ነው፡፡

- አስፈፃሚውን አካል በተመለከተ ማስተማሩንና ሕጉን ማስከበሩን የትራፊክና የፖሊስ አባላቶች በበለጠ ሊአስተ ካክሉት ይችላሉ ብዬ አምናለሁ፡፡
- በአጠቃላይ የእግር መንገዶችን የሚዘጉና ተገቢ ባልሆነ ቦታ እየተገኙ ሕገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ ለሚያከናውኑ ሰዎች የንግድ ማከናወኛ ቦታ ችግር በማይፈጥርበት ሁኔታ ቢሰጣቸው ችግሩ ጨርሶ ባይወገድም በከፍተኛ ደረጃ ሊቃለል ይችላል ብዬ አምናለሁ፡፡

ከመነገጃው ቦታ ውጭ ሲነግዱ ቢገኙ ማንኛውም አይነት ቅጣት ቢፈፀምባቸው ተገቢ ነው እላለሁ፡፡ የመነገጃው ቦታ እንደአስፈላጊነቱ በተለያዩ ቦታዎች በፕላን ክፍልና በቀበሌዎች ቢመረጥና ቢመደብ ግቡን ይመታል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ቁጥጥሩንም ሆነ ሕገ ወጥ ግንባታዎችን የማፍረሱን ኃላፊነት ጨምሮ ለዞኑ ቢሰጥና በቀበሌዎች አማካይነት ተፈፃሚ ቢሆን የሚሻል ይመስለኛል፡፡

<u>የተዘነጋ ነጥብ፦</u>

ለሕይወታችን ዋስትና፣ ለጤናችን ገንቢ፣ ለአእምሮአችን እርካታን ሰጪ እና የአየር ንብረታችንን አዳሽ ለሆኑት ለእጽዋቶች ለምን ትኩረት እንዳልተሰጠው አልገባኝም፡፡

በመሠረቱ ፓርኮችና የእስፖርት ቦታዎች፣ ግሪን ቤልቶች፣ የመንገድ ዳርና የአደባባይ ቦታዎች፣ በከተማው ክልል ላይ መኖር ያለባቸው

የእርሻ ቦታዎች ሁሉ በከተማው ማስተር ፕላን ውስጥ እንደሌሎቹ የአገልግሎት ሰጭዎች ተገቢውን ቦታ በተገቢው መጠን ሰፍሮ መገኘት ነበረበት። ይህ ባለመሆኑ ችግሩ እየጎላ መጥቷል። በአንድ አረፍተ ነገር ለማጠቃለል ዘመናዊ መናፈሻዎችና የስፖርት ቦታዎች በተገቢው ብዛትና ስፋት ከመኖሪያ አካባቢ ጋር በተያያዘ የተሠራም ሆነ የተቀየሰ አለመኖሩ ለፕላን ክፍል የወደፊት እራስምታት መሆኑን ላስታውስ እወዳለሁ።

ጌታቸው ማኅተመሥላሴ

ሰኔ 1 ቀን 1992 ዓ.ም





# የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ

እኛ ኢትዮጵያዊያኖች በቀድሞው ዘመን ማንኛውም ነገር ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ እንደማይሆን የምናምንና በሱም የምንመካ ሕዝቦች እንደነበርን ታሪክ ይመሰክራል።

"ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" የሚለውም ሌላው ማረጋገጫ ነው። እንዳሁኑ እያደርገውና በቀድሞው ዘመን እግዚአብሔር ቀኑን ሙሉ በያንዳንድ ግለሰብ ባለማቋረጥ ሲመሰገን ይውል ነበር። ይኸውም እንዴት ዋልክ ለሚል መልሱ እግዚአብሔር ይመስገን፣ ለሚሰጥ እግዚአብሔር ይስጥልኝ፣ ግራ የገባው ሁሉ እግዚአብሔር ያውቃል በማለት በፈጣሪው ይመካ ነበር።

ከ1966 ዓ.ም ወዲህ ግን አገሪቱን ያስተዳድር የነበረው መንግስት በዘረጋው ስርዓት እግዚአብሔር የተካደበትና የተናቀበት ጊዜ ስለነበር ባለሥልጣኖቹና ተከታዮቻቸው በእብሪት ሁሉም ነገር በኃይላቸው፣ በእውቀታቸው ወይም በብልጠታቸው ተፈፃሚ ለማድረግ ሞከሩ። ጥንታዊና መንፈሳዊ ባሕላችንን ማውደምም አላማቸው ሆነ። ከፊል ሕዝቡንም ከጥቅም ጋር በተያያዘ ዘዴ እግዚአብሔርን ክዶ ከነሱ ጎን እንዲሰለፍ ቢያደርጉም እንዳሰቡት አልቀናቸውም። እብሪታቸው ለዛ ሁሉ እልቂትና እሥር እንዲሁም ረሐብና መሰደድ አበቃ።

"ሁሉንም መዘርዘሩ ለቀባሪዋ አረዷት" እንደተባለው ስለሚሆን ትቸ ዋለሁ። በሥርአት አልበኝነት የተገነባው አገዛዝና ስልጣኔ "ከድጡ ወደ ማጡ" ገብቶ ለአገር ጥፋትና ለሕብረተሰቡ መበላሸት ምቹ ሁኔታ በመፍጠሩ ያሁኑ ጊዜ ጠባያችን ልክ በሁለተኛው የሐዋርያው የጳውሎስ መልክት ወደ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 3 ላይ ከተጠቀሰው

ትንቢት ጋር ፍፁም ተመሳሳይ ሆኖ ይገኛል።

ትንቢቱም፡- "በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንደሚመጣ እወቅ፣ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፣ ገንዘብ የሚወዱ፣ ትምክህተኞች፣ ትእቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይ ታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ እርቅን የማይሰሙ፣ ሐሜተኞች ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነ ውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በትእቢት የተነፉ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፣ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል" ካለ በኋላ "ከእነዚህ ደግሞ ራቅ" በማለት ያስጠነቅቃል። ያሁኑ ጠባያችን በአብዛኛው ከላይ እንደተዘረዘረው መሆኑን የሚክድ ሰው አለ ብዬ ስለማልገምት ሁላችንም በሥራችን ተጸጽተን ለኃያሉ እግዚአብሔር ሕግ ተገዥ በመሆን ከወንጀላችን ነፃ ለመሆን መጸለይ ይኖብርናል።

የመጣው ይምጣ ብለን ከስሕተታችን ባንቆጠብና ከእግዚአብሔር ይቅርታ ባንለምን ቅጣቱ ከበፊቱ ሁሉ የከፋ እንደሚሆን አንጠራጠር።

ከዚህ በፊት በተለያየ ጊዜ በተለያየ መልክ በርካታ ቅጣቶች ደርሰውብናል። ለማስታወስ ያህል፣ ረሐብ፣ ጎርፍ፣ ድርቅ፣ ጦርነት፣ የተለያዩ በሽታዎች፣ የርስ በርስ ጥላቻ፣ የመሳሰሉት ሲሆኑ ቁጣውን እንዲያስታግሥልን ይቅርታና ምሕረትን ከእግዚ አብሔር ከመጠየቅ ይልቅ እጃችንን ወደ ኃያላን መንግስታትንና እርዳታ ሰጭዎች ዘርግተን መለመኑን መረጥን። የተመካንባቸውም ከችግራችን ሊያላቅቁን ባለመቻላቸው ሥጋታችን አሁንም አልተቀነሰም።

በተጨማሪም በአመራር ላይ በተፈጠረው ቀውስ እንዳለፈው ጊዜ





አሁንም እሥራት፣ ቅጣት፣ ስደት፣ ሲከፋም ሕልፈት፣ ንበረት መውረስ፣ ከሥራ መባረር፣ የተለመደ ሆኗል። ረሐብና ልመና ግን ዋና መታወቂያችን እንደሆነ ቀጥሏል።

በተለይም በአሁኑ ጊዜ በሙስና ወንጀል የተዘፈቁት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ የሚለውን ሁኔታ በመፍራት አገር ጥሎ የሚሰደደው ሕዝብ ብዛት ጨመረ እንጂ አልቀነሰም።

ከደርግ አገዛዝ በፊት አገር ጥሎ የሚሰደድ ኢትዮጵያዊ ስለመኖሩ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም የተቸገሩ የውጭ አገር ስደተኞችን ተቀብሎ ከማስተናገድ በቀር።

ጎመን በጤና የሚለው ያ መንፈሰ ጠንካራ ኩሩ ኢትዮጵያዊ ተሰዶና ተዋርዶ ከመኖር በአገሩ ላይ ደሐ ሆኖ መኖርን የሚመርጥ ጨዋ ሕዝብ ነበር። አሁንም ይህ ጨዋነትና የሃገር ፍቅር ባልተማረው ሕዝብ ዘንድ በመጠኑ እንደተጠበቀ ያለ ቢሆንም፣ በዘመን አመጣሹ "የኔ የኔ ነው፣ ያንተም የኔ ነው" በሚለው የስግብግብነት መርሃ ግብር ምክንያት አስጨናቂው ዘመን ሊከሰት ስለሚችል ሁላችንም የችግሩ ተካፋይ መሆናችን አይቀሬ ነው፡ ፡ ስለዚህ ክፉ ሥራችን የሚያመጣው ጠንቅ "ያባት እዳ ለልጅ" እንዲሉ ለልጆቻችን እንዳይተርፍ የአንድ አገር አንድ ሕዝብ ሆነን በፍቅር በለሟ አገራችን ላይ በሰላም ለመኖር በሕብረት እንጣር፡፡ "የሚመካም ሁሉ በእግዚአብሔር ቢመካ" የሚያጣው ነገር የለምና።

# ደድረስ ለእድሜ መጽሔት አባባት

ከሁሉ አስቀድሜ ይህችን ጽሁፍ ለናንተና በክብር ለተጠሩ እንግዶች እንዳሰማ ስለተፈቀደልኝ አመሰግናለሁ፡፡

እንደምታውቁት እኔ የቴክኒክ ባለሙያ እንጅ የታሪክም ሆነ የሥነ-ጽሁፍ ባለሞያ ስላልሆንኩ ለሥህተቶቼ አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡

ይህችን ጽሁፍ ያዘጋጀሁትም አባቴ ክቡር ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ወልደ መስቀል ከአባታቸው ከክቡር ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ መስቀል በቃልና በጽሁፍ ካገኙአቸው እውነተኛ የኢትዮጵያ የታሪክ ማስረጃዎችና እንዲሁም እራሳቸው በስልጣን ላይ በቆዩበት ዘመን በስፋት ከሰበሰቧቸው እውነተኛ ማስረጃዎች ተጨምቀው በአባቴ በክቡር ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ከተዘጋጁት በርካታ መጻሕፍቶች ውስጥ በተለይም ከዝክረ ነገር ውስጥ ለመልዕክቴ ማስተላለፊያ የሚጠቅመኝን በመምረጥ፣ እንዲሁም አባቴ በሕይወት ባሉበት ዘመን ከሰጡኝ ምክርና ትምህርት ጋር በማገናዘብ የተዘጋጀች ማስታወሻ ነች፡፡ የጽሁፌም ርዕስ ኢትዮጵያ ማነች፣ የማንስ ነች፣ የሚል ነው፡፡

ኢትዮጵያ የኛ አገር፣ የኛ የማንነታችን መታወቂያ፣ በነፃነት ኮርተን የምንኖርባት፣ የብልጽግናችን መሰረት፣ የዕኩልነት መብታችንን ያስገደብ የምናስከብርባት አገራችን ኢትዮጵያ መሆኗን ባለመገንዘብ ታሪኳን የሚአጎድፉ፣ ባህሏን የሚንቁ፣ የኢትዮጵያን ቀደምት ስልጣኔ የማያውቁና የሚነቅፉ ሰዎች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ በመሄዱ ከዚህ ስህተታቸው እንዲታረሙ መልዕክቱ በናንተ የታሪክ አስተማሪዎች በኩል እንዲደርሳቸው የቀረበ ማሳሰቢያ ነው፡፡

ታሪክ እንደሚያስረዳን፣ ኢትዮጵያ ተብላ የምትጠራው አገራችን በመንግስትነት የምትታወቀው 1,200 ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት





ጀምሮ ሲሆን፣ ከልደት በኋላ ደግሞ ያለው 1,900 ዘመን ሲጨምር ከ3,000 ዘመን ይበልጣል፡፡

የኢትዮጵያን ገናናነት ለመግለጽ ብንፈልግ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በቂ ማስረጃ ነው፡፡

ለምሳሌ በዜና መዋዕለ ካልእ ምዕራፍ 14 ቁጥር 9 ላይ "ዛሬ በዓለም ላይ ሁሉ ካሉ ነገሥታቶች በፊት ከኢትዮጵያና፣ ከእየሩሳሌም መንግስት በስተቀር ሌላ መንግስት እንዳልነበረ ያረጋግጥልናል፡፡"

ኢትዮጵያን በመንግስትነት የሚቀድማት ቢኖር የግብፁ የፈርኦን መንግስት ብቻ ነው፡፡

ኢትዮጵያን በአውሮፓ ካሉ መንግስታቶች በጥንታዊነት የሚወዳደራት አንድም የለም፡፡

ኢትዮጵያ በሐይማኖቷ የክርስቶስን መንግስት ስትቀበል ከአውሮፓውያኖች ቅድሚያ የነበራት አገር ናት፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም በተለይም በአፍሪካ የራሷ የሆነና የበለፀገ የመነጋገሪያ ቋንቋና የራሷ የሆነ ፊደል ያላት፣ ከሌሎች ፊደልና ቋንቋ ካላቸው አገሮች ጋር የመትወዳደር አገር ናት፡፡

ኢትዮጵያ በሥልጣኔም ደረጃዋ በቀደምትነት ከሚጠቀሱት አንዷ አገር ስትሆን በአፈ ታሪክ ሳይሆን በዓይን የሚታይ በእጅ የሚዳሰስ የታሪክና የስልጣኔ ማስረጃዎትን ማቅረብ የምትችል አገር ናት፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም ታላቅና ኃያል መንግስት ተብለው ከሚጠሩት በ3ኛ ደረጃ ላይ ነበረች፡፡ በኢትዮጵያ ስልጣኔ ባለበት ያዘገመበት ወይም የቆመበት ጊዜ አልነበረም፡፡

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ሕዝቡ በሕግና በሥነ-ሥርዓት እንዲተዳደር

በማሰብ ከአውሮፓ የሥራ አከፋፈል ደንብን አስመጥተው በ1900 ዓ.ም የመንግስታቸውን ሥራ 12 ላይ በመከፈል ለሥልጣኔ የተስማሙትን ሰዎች በመምረጥና ሚኒስትሮችን በማሾም መብ ትና ግዴታቸውን በሚገልጽ መመሪያ ሥራቸውን ቀጥለዋል፡፡

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱም የዳግማዊ ሚኒሊክን ፈለግ በመከተል በዘመኑ ሥልጣኔ አገራችንን አስተዳድረዋል፡፡

በ1898 ዓ.ም የወጣውን የዳግማዊ አፄ ሚኒሊክን የትምህርት አዋጅ ብንመለከት ለዘመናዊ ስልጣኔ የነበረውን ጠንካራ አቅም ያረጋግጣል፡፡

አዋጁም ከዛሬ ጀምሮ ለወደፊት ወንድ ልጆቹንና ሴት ልጆቹን ሁሉ ከ6 ዓመታቸው በኋላ ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይሁን፡፡ ልጅ ያለው ሰው ሁሉ የጽሕፈትና የማንበብ ትምህርት ካላስተማረ መቀጫ 50 ብር ይከፈል፡፡

የንሰሃ አባት የሆንክ ቄስ ሁሉ የንሰሃ ልጅህ ሁሉ ልጆቻቸውን እንዲያስ ተምሩ ምክር፡፡ ምክርህን ካልሰማ ላገሩ ሹም ነግረሕ አስቀጣው፡፡ ባገርህ ያለው'ን የእጅ ሥራ አስተምር ለኑሮው የሚአስፈልገውን ገንዘብ እንዳይቸገር፡ የትምህርት ማስተማሪያ እድሜም ከ6-20 ዓመት ነው" ይላል፡፡

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም የአፄ ምኒልክን አዋጅ መሠረት በማድረግ ትምህርት በስፋት እንዲገነባ አድርገዋል፡፡

በኢትዮጵያ ዘመኑን ከተከተሉ ሥልጣኔዎች ውስጥ አንዱን ለናሙና ብንጠቅስ ከውጭ መንግስታት ሕግ ጋር የተገናዘበና ከአገራችን ፍላጎት ጋር የተጣጣመ ሕገ መንግስት በማርቀቅ ከ1923 ዓ.ም. ወዲህ የሕግ መወሰኛና መምሪያ ምክር ቤት ከፍታለች፡፡

ኢትዮጵያ ባገሯ ላይ ባላት የረጅም ጊዜ የአስተዳደርና የአመራር





ችሎታዋ በዓለም ላይ ባሉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ለምሳሌ በተባበሩት መንግስታት በሊግ ኦፍ ኔሽን፣ በገለልተኛ መንግስታትና በመሳሰሉት ከፍተኛ ተቋሞች ከመሥራች አባሎች አንዷ ለመሆን የበቃች አገር ነች፡፡

ኢትዮጵያ ባላት የረጅም ጊዜ አመራርና የሰከነ የአስተዳደር ችሎታ ለዓለም ድርጅቶች ካበረከተችው ሚዛናዊ ምክር በተጨማሪ በተከታታይ ሰላም አስከባሪ ሁና በመመረጥ ሠራዊቷን በተለያዩ አገሮች ያሰለፈችና ግዴታዋንም በጀግንነት የተወጣች አገር ናት፡፡

ኢትዮጵያ እንኳንስ የራሷን ነፃነት መጠበቅና ማስተዳደር ቀርቶ የሌሎችም አገሮች የነፃነት በር ከፋች የፖለቲካ ሊቅ እንደሆነች ወዳጅም ጠላትም ይመሰክርላታል፡፡

ይህን ሁሉ ገናና ታሪካችንን ትውልዱ በበለጠ በመገንባት ፈንታ ያለንንም በማውደም ላይ ለመሆኑ ምልክቶች ይታያሉ፡፡

ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያ የማን መሆኗን ለተተኪው ትውልድ ማሳወቅ የናንተ የታሪክ መሁሮች ኃላፊነት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

የአገራችን የኢትዮጵያ ታሪክና ባህል እንዲጠፋ ሆን ተብሎ የተጀመረው ደርግ የኮሚኒስትን አገዛዝ በአገራችን ላይ ተግባራዊ ለማድረግ በነበረው ሥር ነቀል ለውጥ እቅድ መሠረት ነው፡፡

በአንደኛ ደረጃ ኃይማኖታችንን በማስካድና በማፈራረስ 2ኛ የንጉሳዊ አገዛዝንና አስተዳደርን በማውደም 3ኛ ዓላማውን ይቃወማሉ የሚላቸውን ታዋቂ ሰዎችን፣ ምሁሮችን፣ ሃብታም ነጋዴዎችን፣ በገጠር ያሉ ባላባቶችን በሐሰት ፕሮፖጋንዳ ጥሩ ታሪካቸውን በማጉደፍና በማዋረድ በሕዝብ እንዲጠሉ፣ እንዲገደሉ፣ እንዲሰደዱ፣ እንዲታሰሩ አደረገ፡፡ ቀጥሎም በመስ ኮቦችና በሌላም ኮሚኒስቶች በሰለጠኑ

ካድሬዎች አማካይነት በዘመኑ በነበሩ ጎልማሶችና ወጣቶች አዕምሮ ውስጥ ሰይጣናዊ ድርጊቶችን በማጎልበት እናትና አባቶቻቸውን ጭምር እንዲገድሉ፣ እርስ በርሳቸውም እንዲገዳደሉ ስልጣን ተሰጥቷቸው ስነለበር ያስርህራኄ ተግባር ላይ እንዳዋሉት በአይናችን አይተናል።

በገሃድ እንደምናውቀው ኢትዮጵያን የሚጠብቃት አንድ ኃያሉ እግዚአብሔር በመሆኑ ለዚህ ያበቋትን ጠላቶችዋን የደመሰሰላት ቢሆንም ያ ጥላቻ አሁንም ከህዝቡ አእምሮ ውስጥ ጨርሶ ባለመጥፋቱ በአንዳንድ የውይይት መድረኮች ላይ ታሪኳንና ባሕሏን የሚያጠፉ እርምጃዎች እየወሰዱና በቴሌቪዥንም ለሕዝብ እየታዩ ነው።

ለምሳሌ ያህል በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት የወጣው የትምህርት አዋጅ ወላጆች ሁሉ ልጆቻቸውን ከ6 ዓመታቸው ጀምሮ እንዲያስተምሩ፡ ፡ ባያስተምሩ 50 ብር ይቀጣሉ እያለ የደሃ ልጅ እስከ አራተኛ ክፍል ብቻ እንዲማር የሃብታም ልጅ እስከ መጨረሻው እንዲማር ነበር የሚፈቀደው ተብሎ በቴሌቪዥን ተነግሯል።

ቀጥሎም ስለ ቋንቋ ውይይት ሲደረግ የአማርኛ ቋንቋ እንደላቲን ቋንቋ ወደፊት የሚሞት ነው አይቀጥልም በማለት ተነግሯል። በምን ቋንቋ እንደሚተኩት ግን አልተናገሩም። የተሻለ መተካት ቀላል አለመሆኑን የተገነዘቡ አይመስለኝም። ማፍረስ ቀላል በመሆኑ የምፈራው ወደ ሃሁ ደረጃ እንዳይመልሱን ነው።

ሌላው፣ አባቶቻችን ያወረሱን ረሐብና ድህነት ብቻ ነው የሚል ነበር፡ ፡ ለመሆኑ ለም የሆነችውን፣ ማርና ወተት የምታዘንበውን የሥልጣኔ መሠረት የተጣለባትን የእርሻ ልማቶችን፣ ኢንዱስ ትሪዎችን፣ ሕንፃዎችንና ሌላም ተቋሞችን ያሟላች ዳር ድንበሯ የተከበረ ኢትዮጵያን ደርግ የወረሰው ከማነው? ከአባቶቻችን አይደለምን? ከዚህ በላይ ምን ያስረክቡ።





ሌላው፣ አሳዛኝ ሁኔታ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ኋላ ቀር ብለው ማንቋሸሻቸው ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እርቆ አስተዋይ ብልህ ሕዝብ ለመሆኑም ከፍ ብሎ የተዘረዘሩት አስደናቂ የሥራ ውጤቶች በቂ ምክስር ናቸው።

በመቀጠልም፣ ስለባሕል ምንነት ተነስቶ ባህል በየጊዜው ተለዋዋጭ ስለሆነ ቋሚነት የለውም አዲስ ነገር ሲመጣ እንደ ፋሽን የሚተካ ነው ተብሏል። ያለንን ጥሩ ባሕል ዋጋ አሳጥቶ በመጤ ባሕል መተካቱ ታሪክ የለሽ አገርና ሕዝብ አያደርገንምን? ደግሞስ ባሕላችንን፣ እራሳችንን የምንንቀው ከማን ባሕል አንሶ ነው?

በመሰረቱ ትውልድ እንዲማር እንዲያውቅ የሚደረገው ያገሩን ጥሩ ታሪክና ባሕል ጠብቆ በተማረው ትምህርት አገሩን አሻሽሎ እንዲገነባ እንጂ ያለውን አፈራርሶ ታሪክ የለሽ እንዲያደርገን አይደለም። ያለውን ጠብቀው በጥሩ ዘመናዊ ባህል እንዲጠቀሙ የማይደክም የለም።

ብዙ ወጣቶች ተወዳጅ ባህላችንን በመንቀፋቸው ሐዘናችን ምን እንደመሰለ ይህች ምሳሌ የበለጠ ታስረዳለች ብዬ እገምታለው። “ላም ወለደች እሳት፣ እንዳትልሳት ፈጃት እንዳትተዋት ልጇ ናት።” በማለትም ንግግሬን ጨርሻለው አመሰግናለሁ።

ኢንጂነር ጌታቸው ማኅተመሥላሴ

## በኢንጂነር ጌታቸው ማህተመስላሴ በተለያዩ ጋዜጦች ላይ በልዩ ልዩ ርዕሶች የተፃፉ አስተያየቶችና የጥናት ጽሑፎች

| ተ.ቁ | የጽሑፍ ርዕስ | ጽሑፍ የቀረበበት ጋዜጣ መጠሪያ | ቀን |
|---|---|---|---|
| 1 | ስለ ማስተር ፕላን ክለሳ ... | (ሪፖርት ለንጉሱ) | 1956-57 ዓ.ም |
| 2 | ስለ ኤሌክትሪክ አውቶቢስ ... | (ሪፖርት ለንጉሱ) | 1956-57 ዓ.ም |
| 3 | ስለ ብሔራዊ ሃብት ልማት ... | (ሪፖርት) | 1957 ዓ.ም |
| 4 | ስለ ክ/ሌ መንግስቱ አምባገነንነት | ተናገር | ሰኔ 8 ቀን 1986ዓ.ም |
| 5 | ስለ ክ/ሌ መንግስቱና ግብረ አበሮቻቸው | ተናገር | ሰኔ 15 ቀን 1986 ዓ.ም |
| 6 | አገር የሚለማው ከህዝብ ፍላጎት ጋር ነው | ተናገር | ሐምሌ 16 ቀን 1986 ዓ.ም |
| 7 | የመጀመሪያው ላንድስኬፕ ... | ምዕራፍ (ጋዜጣ) | ሚያዚያ 27 ቀን 1990 ዓ.ም |
| 8 | ስለ ሠራተኞች ሁኔታ ... | ጦቢያ (ጋዜጣ) | መስከረም 16 ቀን 1992 ዓ.ም |
| 9 | ነጩን ጥቁር ማለት ልማድ ስለሌለኝ | መብረቅ (ጋዜጣ) | መስከረም 10 ቀን 1994 ዓ.ም |
| 10 | የወገን ነፍስ አድን ጥሪ ... | | ህዳር 13 ቀን 1995 ዓ.ም |
| 11 | (ማስተር ፕላን) እተቻለሁ መፍትሄውንም አብሬ አቀርባለሁ .. | ሪፖርተር | ህዳር 30 ቀን 1995 ዓ.ም |
| 12 | "እንደ ብሔራዊ ሃብት ልማት ያለ ክብንያ በብሄት ማቋቋም ይቻላል | ሪፖርተር መጽሔት | ነሐሴ 1995 ዓ.ም |
| 13 | ከዓለም ሕብረተሰብ ተለይቶ ... | ዋስትና (ጋዜጣ) | መጋቢት 1996 ዓ.ም |
| 14 | ይድረስ ለእድሜ መጽሔት አባላት | | መስከረም 8 ቀን 1999 ዓ.ም |
| 15 | የግብርና ጠበብቶች (ማስታወሻ) ... | ሪፖርተር(ጋዜጣ) | ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም |
| 16 | ስለ ኮንዶሚኒየም ... | ሪፖርተር መጽሔት | ጥቅምት 2001 ዓ.ም |
| 17 | የአየር ንብረት ለውጥ (ኪዮቶ) ... | ሸገር (ሬዲዮ) | ሕዳር 7 ቀን 2002 ዓ.ም |
| 18 | የግብርና ባለሙያዎች ወዮታ ... | አዲስ ነገር (ጋዜጣ) | ሰኔ 7 ቀን 2002 ዓ.ም |
| 19 | የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ | | |

በተጨማሪም መንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ስለ ከተማ ዕድገትና ውበት በሚደረጉ የተለያዩ አውደ ጥናቶች ላይ የክብር ተጋባዥ እየሆኑ ገንቢ የሆኑ ሙያዊ አስተያየቶችን ሰጥተዋል፡፡ አሁንም እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

# በባንድስኬፕ አርኪቴክት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ

. . . "ስልክ ተደውሎ ልትታሰር ነው አትምጣ፤ በእንግሊዝ ሃገር የነበሩ ኢትዮጵያውያኖች አትሂድ፣ ሥራ ይዘህ ልጆችህን አሳድግ፣ ዘመዶችህንም አግዝ ብለውት ነበር። የማናችንንም ልመናና ጥያቄ አልሰማም። የሠራሁት ጥፋት የለም። ያደረጉኝን ያድርጉ ብሎ ወደ ኢትዮጵያ መጣ።"

አቶ ሚሊዮን ወ/መስቀል

. . . "በመሠረቱ ሁለት የተለያዩ ነገሮችን በአንድ ላይ ማግኘት ከባድ ነው። ኢንጂነር ጌታቸው ግን ሁለቱን በአንድ ላይ የያዙ ሰው ናቸው። አለቃና አባትነትን በአንድ ላይ።"

ዶክተር አሸናፊ ኃይሌ

. . . "አቶ ጌታቸው ሁሉንም የሚያከብሩ፣ ከነገሥታት ጋር የነበራቸው ግንኙነትና ትልቅነት ሥራ ቦታቸው ላይ ፈጽሞ የማይንፀባረቅ ጨዋ ሰው ናቸው። ባለሙያ እስካመነበት ድረስ ምንም ዓይነት ጫና የማይፈጥሩ ኃላፊ ነበሩ።"

አቶ ገብሩ ሃብተወልድ

ዋጋ 35 ብር

ባናዊ ማተሚያ ቤት